# አዲስ ዘመን

አንድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 069 ኅዳር 9 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይደውሉ

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




## “ሙስና የሀገርን ልማት አጥንቱ ድረስ መጋጥ ከደረሰ አንድ አደገኛ ወረርሽኝ ሆኗል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሙስና የሀገርን ልማት አጥንቱ ድረስ እስከ መጋጥ ከደረሰ አንድ አደገኛ ወረርሽኝ ሆኗል ማለት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰባት አባላት ያሉት የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መዋቀሩንም አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መግለጫ እንደገለጹት፤ ሙስና ሀገርን የሚበላ ነቀዝ ነው፡፡ የሀገርን አንጡራ ሀብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ ነው።

ዋልጌ ባለሥልጣናት፣ በፍቅረ ነዋይ የታወሩ ደላሎች እና ባለሀብቶች አንድ ላይ ሲገጥሙ፤ ከነዚህ የሌብነት

ሙስና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


የሳፋሪኮም ቤተሰብን እንቀላቀል

የሳፋሪኮም ሲም ካርዳችንን

በ30 ብር እንግዛ

15 ብር
70
700 ሜ.ባ
70 ደቂቃ
ከሳፋሪኮም ወደ ሳፋሪኮም

Safaricom
ሳፋሪኮም


## የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ ለአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ የአመለካከት ሥልጠና መስጠት ይገባል

- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ መንግሥት ለአገልግሎት ሰጪና ለአገልግሎት ተቀባይ ጭምር የአመለካከት ለውጥ የሚያመጣ ሥልጠና በመስጠት ችግሩን ከስር ነቅሎ ማውጣት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገለጹ።

የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ አበበ ድረስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ለመብቱ የማይታገል በመሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግር ሲፈጠር ለምን ብሎ የመጠየቅ ባህል የለውም። ስለዚህ ይህንን ለመቅረፍ መንግሥት ለሕዝቡ የአመለካከት ለውጥ የሚያመጣ ሥልጠና በመስጠት ችግሩን ከስር ነቅሎ ማውጣት አለበት።

በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል ያለውን ግንኙነት ብንመለከት አገልግሎት ተቀባዩ ፈጣን ምላሽ ይፈልጋል። አገልግሎት ሰጪው ደግሞ ከመመሪያና ከአሰራር አንፃር አገልግሎት የሚፈልገው አካል ያላሟላው

የመልካም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡ ገባቡ ገብሬ

## ለአፋር ክልል ለተፈናቀሉ ዜጎች የ285 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደረገ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በአፋር ክልል በጦርነቱ ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜጎች እና ለሴፍቲኔት ፕሮግራም የሚውል 285 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ።

ድጋፉን የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ሃጂ አወል አርባ አስረክበዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ ለችግር የተጋለጡና በአፋር የሚገኙ 24 ሺህ 200 ተፈናቃዮችን ለማቋቋም የሚውል 170 ሚሊዮን ብር ተመድቧል።

በተጨማሪ በአፋር ክልል በከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክትና በአሳይታ ካምፕ የሚገኙ ስደተኞችን ለመደገፍ የሚውል 115 ሚሊዮን 198 ሺህ ብር መመደቡን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ለአፋር ክልል ድጋፍ የሚውል ከ285 ሚሊዮን ብር በላይ መመደቡንና፤ በቀጣይም ለጋሽ አገራትን በማስተባበር በክልሉ የድህረ ጦርነት ማገገሚያ ዕቅድ በማዘጋጀት ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለአፋር ክልል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

## “የቴሌኮም ዘርፉ ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ኢትዮጵያን ወደእድገት ማማ የሚወስዱ ናቸው”

- አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የቴሌኮም ዘርፉን የሚቀላቀል ሶስተኛ ኦፕሬተር እንዲገባ መፈቀዱ እና ኢትዮ- ቴሌኮምንም 40 በመቶ ድርሻ እንዲሸጥ መወሰኑ አዎንታዊ ተጽእኖ በመፍጠር ኢትዮጵያ በእድገት ማማ እንድትጓዝ እንደሚያደርጋት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ ገለጹ። የኢትዮጵያ ሰላም ለዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮችም መተማመኛ እንደሚፈጥር ገልጸዋል፡፡

አቶ ዘመዴነህ መንግሥት ኢትዮ - ቴሌኮምን በከፊል ወደ ግል ለማዘዋወር እና አዲስ ኦፕሬተር ለማስገባት ጨረታ ይፉ ማድረጉን አስመልክተው ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ ተግባሩ የኢትዮ - ቴሌኮምን ተወዳዳሪነት

የቴሌኮም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደብኛ ክላሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565





የሰላም ስምምነቱን የሚቃወም ከጦርነት ትርፍ የሚያገኝ ብቻ ነው

ገጽ 3

# ከ353 ሺህ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የበጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ከ246 ሺህ በላይ በጎ ፍቃደኞችን በማሳተፍ ከ353 ሺህ በላይ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያድረግ የበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የበጋ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስጀመርያ ሥነሥርዓት ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ "በጎ ፈቃደኝነት አያጎድልም፤ በመስጠት የሚጎልብን ነገር የለም፤ በጎ ፈቃደኝነት ለራሳችን የመንፈስ ደስታ የሚሰጥ ለሌሎች ደግሞ ችግሮቻቸውን የሚያቃልል በመሆኑ ሁሉም ሰው የበጎ ፍቃድ ሥራ ላይ መሳተፍ አለበት" ።

በጎፈቃደኝነት ቅደመ ሁኔታዎች የሉትም ያሉት ከንቲባዋ፣ በጎ በማድረግ የበጎ ፈቃድ ሥራውን ማጠናከር ይገባል ብለዋል። የኢትዮጵያን ብልፅግናም ልናሳካ የምንችለው በዚሁ መንገድ ነው ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

"ሁሉም ነገር በክፍያ መሆን የሚችልበት አገር ላይ አይደለንም፤ በጎነትን እንደባህል ይዞ የሚቀጥል ኅብረተሰብ መገንባት ያስፈልጋል" የበጎ ፈቃድ ሥራው እግረ መንገዱን አዕምሮንም ጭምር የሚገነባ መሆኑንም ከንቲባ አዳነች አቤቤ ጠቅሰዋል።

"የበጎ ፍቃድ ሥራ ኑሮ ለጨለማባቸው ተስፋ የሚፈነጥቅ በመሆኑ በታማኝነት እና በቅንነት አገልግሉ" ሲሉም ለበጎ ፈቃደኞች መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከንቲባዋ በማህበራዊ ሚዲያ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት "በበጎ ፍቃድ ስራዎች የበኩላችንን በጎ አሻራ እንድናሳርፍና የበጎነትን በረከት እንድንቋደስ ጥሪዬን አቀርባለሁ" ሲሉ ገልጸዋል፡፡

246 ሺህ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች በከተማዋ በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለመሳተፍ ስምሪት መውሰዳቸውን ከንቲባዋ ገልጸዋል። በጎ ፍቃደኝነት በከተማዋ ባህል እንዲሆን ባለፉት ዓመታት በልዩ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት ሲሰራ መቆየቱን ከንቲባዋ አንስተዋል፡፡

ከንቲባዋ በመልዕክታቸው "በጎነት አያጎድልም፤ የበጎ አድራጊዎች ሃሳብ፣ ተግባር፣ ጉልበት፣ በገንዘብ ከሚተመን ፕሮጀክት በላይ ነው፤ ማህበራዊ ትስስርን አጠናክሮ ትውልድ ያንፃል፤ አገር ይገነባል" ብለዋል፡፡

በዚህ የበጎ ፍቃድ ሥራ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ፣ የአካባቢ ፅዳት፣ የችግኝ መንከባከብ እንዲሁም ወደ 10 ሺህ ገደማ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የበጋ የማጠናከሪያ ትምህርት ይሰጣል።

ከዚህም ባሻገር ወሰን እና ድንበር የለሽ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውጭ ባሉ አካባቢዎች የአርሶ አደሩን ምርት በመሰብሰብ፣ የደም ልገሳ እንዲሁም የቤት እድሳት እና ሌሎች የበጎ ፍቃድ ሥራዎች ይከናወናሉ። በዚህም ሁለት ቢሊዮን ብር ወጪን ለማዳን የሚያስችል የበጎ ፍቃድ ሥራ እንደሚከናወንም ተጠቁሟል።

ባለሀብቶች የጀመሩትን ቀና ትብብር እንዲያጠናክሩ እና አመራሮችም ክትትል እና ድጋፍ በማጠናከር የበጎ ፍቃድ ሥራውን በተሻለ ደረጃ ማከናወን እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ በበጎ ፍቃደኛ ባለሀብቶች የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ትናንት በይፋ አስጀምረዋል፡፡ እያንዳንዳቸው ባለ አራት ወለል ያላቸው አራት ህንፃዎችን በጠቅላላ 160 ቤቶችን የሚይዝ የቤት ግንባታ ነው በባለሀብቶቹ ወጪ ግንባታቸው የተጀመረው፡፡

የቤቶቹን ግንባታ ትናንት በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በይፋ ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ "ቤት ያረጃል፤ ይፈርሳል አስተሳሰቡ ግን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል" ብለዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ጨምረውም በዚህ የበጎ ፍቃድ ተግባር ላይ ተሳታፊ የሆኑ ባለሀብቶች መበልፀግ የምንችለው ሕዝባችንን ይዘን ነው የሚል እሳቤን በመያዝ እያደረጉ ላለው የድጋፍ ተግባርም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።



# ለኢትዮጵያ እድገት ወጣቱ የአንበሳውን ድርሻ እንዲወጣ ማህበሩ አሳሰበ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ለኢትዮጵያ ዘላቂ እድገት ወጣቱ የአንበሳውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል ሲሉ የኢትዮጵያ አረጋውያንና ጡረተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ገለጹ:: ከመጠላለፍ አባዜ በመውጣት የኢትዮጵያን ብልፅግና ማረጋገጥ እንደሚገባም አሳስበዋል::

በዓለማችን ለ32ኛ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ31ኛ ጊዜ በተከበረው የአረጋውያን በዓል የማጠቃለያ መድረክ ሰሞኑን ሲካሄድ የአዲስ አበባ አረጋውያን ማህበር ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ እና የኢትዮጵያ አረጋውያንና ጡረተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ክፍሉ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን ለማሳደግ ከተፈለገ ከመተቻቸትና ከመነቃቀፍ መንፈስ በመውጣት የሀገራችንን ብልፅግና ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሁሉም ሰው በመደጋገፍ ሲተባበር እንጂ በአንድና ሁለት ሰዎች ጥረት ብቻ ሀገርን ማበልጸግ እንደማይቻል የገለጹት አቶ ጌታቸው፤ ከዚህ አኳያ ወጣቱ ትውልድ ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና በምታደርገው ጉዞ የአንበሳውን ድርሻ መወጣት አለበት ብለዋል::

እንደ አቶ ጌታቸው ገለፃ፤ ወጣቱ እናቶቹና አባቶቹ ያቆዩለትን ሀገር በመጠበቅ ወደፊት ሊያሻግር ይገባዋል:: መንግሥት ላይ ስህተት ከመፈለግም በስራ በማገዝ ሀገርን ማስቀጠል ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅበታል::

የአዲስ አበባ ሴቶች የህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዋ ዶክተር ሃና የሺንጉስ በበኩላቸው፣ ሀገርን መጥቀም የሚሻ ሁሉ ሀገርን ትናንትን ከበዛ መከራ አሳልፈው ዛሬ ያደረሱ አረጋውያንን ውለታ ሊያስብና ሊያከብር ይገባል ብለዋል::

እንደ ዶክተር ሃና ፤ ሀገርን ማበልጸግ እና ማሻገር ካስፈለገ አረጋውያንን ይዞ መሆን ይገባዋል:: ሀገር ከማንኛውም ፍላጎት በላይ ትበልጣለችና በዓሉን ማጠቃለል ማለት አከባበሩን እንጂ አረጋውያን መተው አይደለም::

31ኛው የአረጋውያን በዓል በሁሉም ክፍለከተሞች በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር መቆየቱን የገለጹት ዶክተር ሃና፤ ማጠቃለያውም ለበዓሉ ስኬታማነት የሲቪክ ማህበራት ማመስገኛ መሆኑን በመግለፅ ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር አረጋውያንን ማክበር እንደሚያስፈልግም መልእክታቸውን አስተላልፈዋል::

በዝግጅቱ በአረጋውያን በዓል አከባበሩ ላይ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላት ምስጋና የተሰጠበት ሲሆን፤ በመርሀግብሩ ላይ የሀገር ሽማግሌዎች የመንግሥት አመራሮች እንዲሁም ከየክፍከተማው የተውጣጡ ማህበራት የታደሙ ሲሆን አባቶቹ ምርቃታቸውን እንዲሁም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል::



# የኢትዮ- ኬንያ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮ- ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ መስመር እና የኮንቨርተር ማከፋፈያ ጣቢያ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ጀምሯል፡፡

የኢትዮ - ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር ትናንት በይፋ ኃይል ማስተላለፍ የጀመረ ሲሆን በዓመት እስከ አንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማስገባት አቅም አለው፡፡ እንዲሁም ከኬንያ አልፎ ከታንዛኒያ እስከ ደቡብ አፍሪካ ላሉት ሀገራት እስከ ሁለት ሺህ ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ አቅም ያለው ነው፡፡

የኢትዮ- ኬንያ የኃይል ማስተላለፊያ መስመርና ኮንቨርተር ጣቢያ ፕሮጀክት ለአማካሪ ድርጅቱ፣ ለካሳ ክፍያና የተሰረቁ መሰረተ ልማቶችን ለመተካት የወጣውን ወጪ ጨምሮ ወደ አምስት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪ ተደርጎበታል፡፡ ከዚህ ውስጥ 214 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላሩ ለኮንቨርተር ስቴሽኑና ለግራውንድ ኤሌክትሮድ መስመር የግንባታ ሥራ እንዲሁም 120 ሚሊዮን ዶላሩ ደግሞ ለማስተላለፊያ መስመሩ የዋለ ነው፡፡

የኢትዮ- ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የማስተላለፊያ መስመር የግንባታ ሥራ "CET" በተሰኘ የቻይና ኩባንያ የተከናወነ ሲሆን የኮንቨርተር ማከፋፈያ ጣቢያውና የግራውንድ ኤሌክትሮድ መስመሩ ደግሞ ሲመንስ በተሰኘ ኩባንያ ተከናውኗል፡፡

በኢትዮጵያ በኩል የተዘረጋው የማስተላለፊያ መስመር እና የፕሮቴክሽንና የዳታ ኮሙዩኒኬሽን መስመር (ኦፕቲካል ግራውንድ ፋይበር) 440 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን 994 የከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ የብረት ታወሮች አሉት።

ኢትዮጵያ የምታስተላልፈው ኃይል ያልተቆራረጠና አስተማማኝ እንዲሆን የሚያግዙ ተግባራትን ያጠናቀቀች ሲሆን በኬንያ በኩል ተመሳሳይ ሥራዎች ተሰርተው በቅርቡ ወደተግባር እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡

የማስተላለፊያ መስመሩ ከደቡብ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የወላይታ፣ ጋሞ እና ኮንሶ ዞን እንዲሁም ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቦረና ዞን አቋርጦ ነው ወደ ኬንያ ኃይል የሚያስተላልፈው።

በማስተላለፊያ መስመሩ ላይ ኃይል የማስተላለፍ የሙከራ ሥራ ከጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ሲከናወን ቆይቷል፡፡

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ከሱዳን እና ከጅቡቲ ጋር የኃይል ሽያጭ እያካሔደች ሲሆን ከሶማሌላንድ፣ ታንዛኒያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ለማከናወን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማለች።

ባለፈው ዓመት ለሱዳን እና ለጅቡቲ ኤክስፖርት ከተደረገው የኤሌክትሪክ ኃይል 95 ነጥብ 4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶሊር ገቢ ተገኝቷል፡፡

# ለሀገራዊ ብልጽግና መደላድል ለመፍጠር የመረጃ ሥርዓቱን እያዘመነ መሆኑን አገልግሎቱ አስታወቀ

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ፡- የበለጸገች ሀገር ለመገንባት የሚያስችሉ ፖሊስዎችና ስትራቴጅዎችን ለመቅረጽ የመረጃ ሥርዓቱን ማዘመን ላይ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

"በተጠናከረ ዘመናዊ መረጃ ሥርዓት ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የአፍሪካን ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ "በሚል መሪ ቃል ዛሬ የሚከበረውን የአፍሪካ ስታስቲክስ ቀን ምክንያት በማድረግ ትናንት የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር በከር ሻሌ በፓናል ውይይቱ ላይ እንደገለጹት በዓሉን ምክንያት በማድረግ የሚደረጉ ውይይቶች ዘመናዊ ስታስቲክስ መረጃ ሥርዓት አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አሰረጫጨት ላይ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፡፡ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲጨምር በማድረግ በተናበቡ መረጃዎች የበለጸገች ሀገር ለመገንባት ያግዛል፡፡

ማንኛውም ሀገር ለግብርና ዘርፍ መጨመር ፣ ለደህንነት መጠን ልየታ፣ የሥራ አጥነት መጠን ፣ የገበያ ዋጋ ጥናቶች በሚደረጉበት ወቅት መንግሥት የተሻሉ ነገሮችን በማስቀጠል ክፍተቶች ሲኖሩ ለመሙላት ጥራት ያለው ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት አያያዝ ለማረጋገጥ የተቋሙ ድርሻ ከፍተኛ ነው ብለዋል ፡፡

በአስር ዓመታት ልዩነት እንደ ሀገር የሚካሄደው ሕዝብና ቤት ቆጠራ በተለያዩ ምክንያቶች ተራዝሟል ያሉት ዶክተር በከር፤ ተቋሙ የመረጃ ሥርዓቱን በማዘመን፣ ከመረጃ ሰጪ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ያለውን ትስስር በማጠናከር የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበክቱ የማድረግ ስራዎች ይሰራል ብለዋል፡፡ ዘመኑ ወደሚፈልገው ስታስቲክስ መረጃ ሥርዓት ለማሻገር በትኩረት እንደሚሰራም ገልጸዋል ፡፡

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ነመራ ገበየሁ በበኩላቸው መረጃ ከግለሰብ ሕይወት ጀምሮ ሕዝብና መንግሥትን ለማገናኘት የሚያስችል ነው፡፡ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ፓናል ውይይቱ መካሄዱ ስለመረጃ አያያዝና አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ ስለሚፈጥር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል፡፡

ለፖሊሲና ስትራቴጅ ቀረጻ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በማመንጨት ኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት ለ60 ዓመት የሚያበረታታ ስራ ሲሰራ መቆየቱን አስታውሰው ተቋሙን ከዚህ የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ በመንግሥት የተጀመሩ ሪፎርም ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሀገርም ሆነ እንደ አፍሪካም ያለው የመረጃ አያያዝ ብዙ ይቀረዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሪፎርሙን ለማጠናከር ጥራቱን የጠበቀ መረጃ አሰባሰብ አደረጃጀትና አሰረጫጨት ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል መንግስት ያለውን መረጃ እንዲናበቡ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በዓለም ገንዘብ ተቋም የተቋማትና ፋይናንስ ምጣኔ ፕሮግራም ኃላፊ ሚስተር ማሪዮስ ቪሲማንታስ ኢትዮጵያ የአስር ዓመት እቅዷን ለማሳካት ጥረት በምታደርግበት ወቅት ኮቪድ ወረርሽኝ፣ ግጭቶች ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮች በመኖራቸው እነዚህን ችግሮች ለማሸነፍ ጊዜውን የጠበቀ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ያስፈልጋታል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት የሥርዓተ ጾታ ማካተት ዳይሬክተር ወይዘሮ ሶርሴ ጉተማ ሥርዓተ ጾታን መሰረት ያደረገ የሀብት ባለቤትነት ጥናት በፓናል ውይይቱ ላይ አቅርበዋል፡፡

ወንዶች አንድ ነጥብ አምስት ትሪሊዮን ብር ሴቶች አንድ ነጥብ ሶስት ትሪሊዮን ብር የሀብት ባለቤትነት እንዳላቸው ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ሴቶች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ ሚና ስለሚኖራቸው የታየውን ልዩነት ለማጥበብ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት በዘመናዊ መረጃ ሥርዓት በመታገዝ መረጃን አመንጭቶ ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እንደሚሰራ አብራርተዋል፡፡

# ተመጣጣኝ የሀብት ፍሰት የሚኖረው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ግቦችን ማሳካት ሲቻል መሆኑ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በዜጎች መካከል ተመጣጣኝ ሀብት ፍሰት እንዲኖር በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተቀመጡ ግቦችን ማሳካት ሲቻል ነው ሲሉ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ገለጹ:: አምስተኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ንግድ ትርኢት ትናንት ተከፍቷል::

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ትናንት አምስተኛውን አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ንግድ ትርኢት በከፈቱበት ወቅት "እንደ አገር የሥራ አጥነት እና የኑሮ ውድነት ችግሮችን መፍታት እንዲሁም በዜጎች መካከል ተመጣጣኝ የሆነ ሀብት ፍሰት እንዲኖር ማድረግ የሚቻለው በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ እናሳካቸዋለን ብለን ያስቀመጥናቸውን ግቦች በተሟላ መንገድ ማሳካት ሲቻል ነው" ሲሉ ተናግረዋል::

ኢኮኖሚው ጤናማና ተወዳዳሪ ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በኢኮኖሚው ውስጥ የግል ሴክተሩ ሚናውን በተሟላ መንገድ መወጣት ሲችል እንደሆነ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ለዚህ ደግሞ የተደራጀ ማህበረሰብ መኖሩ አስፈላጊ እንደሆነ አመላክተዋል:: መንግሥት ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት፣ መሠረተ ልማቶችን በማቅረብና ለሥራ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ረገድ ለአምራች ዘርፉ በተለይም በግሉ ዘርፍ የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠር ትልቅ ኃላፊነት አለበት ነው ያሉት::

ከኢንዱስትሪዎች ጋር ያለው ትስስር ለምርታማነት አስተዋጽኦ እንዳለው የገለጹት ሚኒስትሩ፤ መንግሥት በኢንዱስትሪ ፖሊሲው የግሉ ሴክተር ችግሮችን በመፍታት የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን እያበረታታ እንዳለ ጠቅሰዋል:: የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዘርፉን ለማገዝ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆኑንና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት እየሰራ እንዳለ አመላክተዋል::



በዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በዘርፉ አቅምን ማጎልበት እና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል እንደሚገባም ገልጸዋል:: የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚያዘጋጃቸው የንግድ ትርዒቶች ለስትራቴጂክ አቅዶች ማሳኪያ አንዱ መንገድ እንደሆነ ጠቁመዋል:: ትርዒቱ ብሔራዊ የኢኮኖሚ እቅድ ለማሳካት አጋዥ ከሆኑ ሁነቶች ውስጥ እንደሆነም ነው የተናገሩት::

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል:: በተደረጉ እንቅስቃሴዎች በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ያሉትን በርካታ ችግሮች ለማቃለል ትልቅ እድል ተገኝቷል::

ንቅናቄው የአንድ ዓመት ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥሉት አስር ዓመታት የሚቆይ በመሆኑ በተያዘው ዓመት የበርካታ ኢንዱስትሪዎችን ችግር ለመፍታትና በዘርፉ ሰፊ የሥራ እድል ለመፍጠር ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ገቢ ምርቶችን በመተካቱ ረገድ እንዲሁም የኤክስፖርት ድርሻን በማሳደግ ረገድ ጉልህ ሚና ያላቸው ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው::

የዚህ ሥራ አካል የሆነውና ከግል ሴክተሩ የሚጠበቀውን ትልቁን ስራ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እየተወጣ እንዳለና የተጀመረው የንግድ ትርዒትም የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በቴክኖሎጂና ገበያ ትስስር ለመፍጠር፤ በአገር ውስጥ ያሉትን ሰፊ እድሎች እንዲጠቀሙ በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንደሆነም ጠቅሰዋል::

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው፤ የንግድ ትርዒቱ ለግል አምራቾችና ነጋዴዎች ያለው ጠቀሜታ የጎላ እንደሆነ ጠቁመዋል:: አምራቾችንና ኩባንያዎችን ከማነቃቃት ባሻገርም በንግድ ትርዒቱ በርካታ የውጭ አገራት አምራቾችና ድርጅቶች የሚሳተፉበት እንደመሆኑ ለአገር ውስጥ አምራቾች ጥሩ የልምድ መቅሰሚያ ሁነት እንደሆነ ተናግረዋል::

ንግድ ትርኢት "manufacturing for enhanced employment" በሚል መሪ ቃል እስከ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል የሚካሄድ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ ዩጋንዳ፣ ህንድ፣ ጆርዳን፣ ፓኪስታን ሳኡዲ አርቢያ፣ ቱርክ፣ የተባበሩት አረብ ኢሜሬትስና ቻይና ተሳታፊ አገራት ሆነዋል::

በንግድ ትርዒቱ ላይ፣ በኢንዱስትሪ፣ በቴክኖሎጂ፣ በአውቶሞቲቭና በልዩ ልዩ አምራችነት ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ለገበያ እንደሚያቀርቡ ለማወቅ ተችሏል::



# የሰላም ስምምነቱን የሚቃወም ከጦርነት ትርፍ የሚያገኝ ብቻ ነው

**መሰረት ገ/ዮሃንስ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተፈረመውን የሰላም ስምምነት የሚቃወሙ አንዳንድ ዲያስፖራ አባላት እና አክቲቪስቶች ከጦርነት የሚያተርፉ ናቸው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የፀጥታና ደህንነት ሃላፊ ገለጹ።

የትዴፓ የፀጥታና ደህንነት ሃላፊ ኮሎኔል ፍስህ ገብረመድህን ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ በውጭ ሀገር ተቀምጠው የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ አንዳንድ አካላት እነሱ ከጦርነት እንጂ ከሰላም ትርፍ እንደማያገኙ ስለሚያውቁ ነው ብለዋል።

ኮሎኔል ፍስህ እንደገለጹት፣ እነዚህ የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ አካላት በሀገሪቷ ሰላም ከሰፈነ ለነሱ የገቢ ምንጫቸው ስለሚደርቅ ሁል ጊዜ የጦርነት አዙሪት እንዲቀጥል ይፈልጋሉ፡፡


እነዚህ አካላት ይህ ጦርነት ከቆመ ገቢያቸው አብሮ ይቆማል ፣ ጥዋትና ማታ ያልተፈጠረ እየፃፉ፣ ሰልፍ እየወጡ፣ ሩቅ ሁነው በጦርነት ገፈት ቀማሽ በሆነው ህዝብ ቢዝነስ የሚሰሩ ናቸው ያሉት ኮሎኔል ፍስህ፤ እነሱ እያሰቡ ያሉት በዩቱብ እና ሌሎች ማህበራዊ ትስስሮች የሚያገኙትን ገንዘብ ብቻ ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም የሰላም ስምምነቱ ኡደት ምንድነው ብለው ከመጠየቅ ይልቅ ትክክል አይደለም ብለው መቃወም ነው የሚጠቅማቸው ፣ ይህ ደግሞ ለጥቅማቸው ብቻ ነው ፣ ከዚህ ባለፈ ለህዝብ የሚጠቅም ስራ የመስራት ፍላጎት የላቸውም ብለዋል።

ይህ ችግር በትግራይ ብቻ ሳይሆን በአፋርና አማራ ክልሎች የተስተዋለ ነገር ነው፣ በዚህ ጦርነት የመድሃኒት አቅርቦት የለም ፣ ሆኖም የነሱ ልጆች አልሞቱም ፣ አልተቸገሩም ፣ እነሱ የሰላም አየር እየተነፈሱ ነው እሳት እያቀጣጠሉ ያሉት ፣ ይህንን የትግራይ ሕዝብ ሊያውቀውና ሊነቃ ይገባል ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ ኮሎኔል ፍስህ ገለጻ፤ በተደጋጋሚ ጦርነት ምክንያት የትግራይ ወጣት ረግፏል ፣ ወጣት ብቻ ሳይሆን ሽማግሌ እና ህጻናት በዚ ጦርነት ተጎድተዋል፣ ብዙ የአካል ጉድለት ደርሷል፤ ከዚህ በላይ በጦርነት ውስጥ መቆየት ከባድ በመሆኑ የሰላም ስምምነቱ ወሳኝ ነው።ስለዚህ ይህ ስምምነት እንዲፈርስና የትግራይ ሕዝብ መልሶ ወደጦርነት አዙሪት እንዲገባ የሚፈልጉ ሃይሎችን በቃችሁ ማለት ይገባል ብለዋል፡፡

ዜና



አቶ ሀብታሙ ግርማ



አቶ አበበ ድረስ



ወይዘሮ ፍናት ወንድራድ

# የመልካም አስተዳደር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ነገር ይኖራል። ይህን ጊዜ አገልግሎት ሰጪው አገልግሎት ሲሰጥ ገንዘብ የሚፈልግበት ሁኔታ አለ።

ከዚህም አልፎ አገልግሎት ለመስጠት በቀጥታ ገንዘብ የሚጠይቁ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች አሉ ያት አቶ አበበ፣ ሆኖም ይህ ከተቋም ተቋም ይለያያል ብለዋል። ባለጉዳይ ደግሞ መብቱን ከማስጠበቅ ይልቅ የሆነ ነገር ሰጥቶ በአፋጣኝ የሚፈልገው እንዲፈጸምለት ይፈልጋል ሲሉም አክለዋል።

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመቅረፍ ዋናው የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲኖር ማስቻል ነው። ነገር ግን ይሄ በአንድ ጊዜ የሚመጣ ሳይሆን ተከታታይ የህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠርን ይጠይቃል። ሕዝቡ ደግሞ የሚፈልገውን አገልግሎት በገንዘብ ከማግኘት ይልቅ ገንዘብ አምጣ የሚለውን ግለሰብ በመጠቆም በህጋዊ መንገድ ጉዳዩን ለመፍታት መጣር አለበት።

አቶ አበበ እንዳሉት ህዝቡ ከተቋማቱ ማግኘት የሚገባውን መረጃና አገልግሎት ለማግኘት መታገል አለበት። ይህን ለማድረግ መንግሥት የአሰራር ሰንሰለቱን ማስተካከል፤ በተዋረድ ሥልጣና መስጠትና በተጨባጭ የአስተዳደር ችግር የተገኘባቸውን የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ መቅጣት አለበት፤ አሰራሩንም ማሻሻል ይኖርበታል።

ለዚህ ሁሉ የመልካም አስተዳደር እና የሌብነት ችግሮች የዳረገን የሚወሰደው እርምጃ ቀላልና ለሌሎች ትምህርት የሚሰጥ ባለመሆኑ ነው የሚሉት አቶ አበበ፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ ሁሉም በየድርሻው ካልታገለ ለውጥ ሊመጣ አይችልም ብለዋል።

ወይዘሮ ፍኖት ወንድራድ በበኩላቸው፤ መንግሥት ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስቀምጣቸው አካላት በአብዛኛው የተቀመጡበትን ኃላፊነት የመወጣት አቅማቸው ደካማ ነው። ለዚህ ደግሞ በኃላፊነት የሚቀመጡ ሰዎችን የሚመርጡ አካላት እነማን እንደሆኑና ማን እንደመረጣቸው የማይታወቅ በመሆኑ ነው ብለዋል።

አመራረጡ የቡድንና የትውውቅ በመሆኑ ለመንግሥት የአሰራር ሂደት እንቅፋት እንዲኖረው አድርጓል ያሉት ወይዘሮ ፍኖት፤ ችግሩ ያለው የአመራረጥ ሂደቱ ላይ በመሆኑ መንግሥት እነዚህ አካላት የሚመረጡበት ቦታ በመሄድ ማን መራጭና ማን ተመራጭ እንደሆነ ማጣራት አለበት። ይህ ከሆነ አሁን የሚታዩ ችግሮች የማይቀረፉበት ሁኔታ አይኖርም ብለዋል።

ከአስር ዓመት በላይ ጉዳይ አስፈፃሚ ነበርኩ ያሉት ደግሞ አቶ ሀብታሙ ግርማ ናቸው። በዚያ ወቅት በመንግሥት መስሪያ ቤቶች የመልካም አስተዳደር ጉዳይ በስፋት ይታይ ነበር። በዚህም ተገልጋይ ለእንግልት፣ ለጉቦና ለተለያዩ ችግሮች ሲጋለጡ እመለከት ነበር ብለዋል።

አሁን ግን ለመገልገል የሚያስፈልጉህን ዝግጅት አድርገህ ከመጣህ የምትፈልገውን አገልግሎት አግኝተህ መውጣት ትችላለህ ። ይሄም ከለውጡ መንግሥት በኋላ የመጣ የአሰራር ለውጥ ነው። ነገር ግን የመልካም አስተዳደር ችግር የለም ማለት አይቻልም። ይህን ችግር ሰራተኞች ላይ ብቻ ጣት መጠቆም ተገቢ አይደለም ብለዋል።

ለሰራተኞቹ መበላሸት ተጠያቂው አገልግሎት ፈላጊው ራሱ ጭምር በመሆኑ መንግሥት የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ለአገልግሎት ሰጪው ብቻ ሳይሆን ለአገልግሎት ፈላጊውም ጭምር ሥልጠና መስጠት ይኖርበታል ብለዋል።

# “ሙስና የሀገርን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ፊታውራሪዎች ጀርባ ብዛት ያላቸው ዜጎች መሰለፍ ሲጀምሩ ሙስና የተባለው ነቀዝ ሀገርን እንደ ወረርሽኝ ያጠቃታል ብለዋል።

ሙስና ሀገርን ሊያፈርስ የሚችል የደህንነት ሥጋት መሆኑን ያስመሰከሩ ሀገሮችን በዘመናችን አይተናል፡፡ የአደንዛዥ ዕጽ፣ የኮንትሮባንድ፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ፣ የንግድ ማጭበርበር ሙስናን ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ይፈልጉታል ብለዋል፡፡

በመግለጫው እንዳስታወቁት፤ በዓለማችን የተጀመሩ ጦርነቶች እንዳይጠናቀቁ፤ ግጭቶች እንዳይበርዱ፣ ሕዝቦች እርስ በርስ እንዲጋጩ፣ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ሙሰኞች ከዚህ አይነት ቀውሶች አትራፊ ስለሆኑ ነው፡፡

ሙስና ዛሬ የሀገራችን የደህንነት ሥጋት ሆኗል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አስሮ ለመያዝ ከጠላቶቻችን እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው ሲሉ በመግለጫው አስታውቀዋል።

የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

ሕዝቡ በተለያዩ ጊዜያት በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው፡፡ ከሕዝብ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ከጸጥታ ሥጋቶች እኩል ሙስና ለብልጽግና ጉዟችን ዋናው እንቅፋት መሆኑን አንስቷል ሲሉ ጠቁመዋል።

ዶክተር ዐቢይ እንዳስታወቁት፤ መንግሥት በየደረጃው የሚገኘውን መዋቅር በመፈተሽ፣ አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ ሥራዎችን እያሳለጠ ነው። ሥራዎችን ከእጅ ንክኪ ነጻ በማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ አመራሮችንና ሌሎች ተዋንያንን ለሕግ በማቅረብ፣ ሙስና ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠርለት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ነገር ግን ሀገራችን ያጋጠማትን ጦርነትና ኮሮናን የመሳሰሉ ወረርሽኞች የመንግሥትን ትኩረት ወስደዋል ብለው ያሰቡ ሙሰኞች፣ በየቦታው ተሰግስገውና ኔት ወርክ ዘርግተው፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት እየሠሩ መሆናቸውን በዝርዝር የቀረበው የጥናት ሪፖርት ያሳያል ብለዋል፡፡

መንግሥት በጸጥታው ዘርፍ እንዳደረገው ሁሉ በሙስና ላይ ጠንካራና የማያዳግም ኦፕሬሽን ማድረግ እንዳለበት የጥናቱ ውጤትና የሕዝብ ውይይቱ ግምገማ እንዳመላከተ በመግለጫው ተጠቁሟል።

በአንድ በኩል የመንግሥት ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ለሙስና ያላቸውን ተጋላጭነት የማጥፋት ሥራ ይሠራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሙስና ተዋንያንን የማጋለጥና በሕግ የመጠየቅ ተግባር ይከናወናል ሲሉ አስታውቀዋል።

ሙስናን ከሥር ከመሠረቱ ለመንቀል እንዲቻል ከሕግና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ የሙስና ተዋንያን ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ እርምጃ ያስፈልጋል፡፡ መንግሥት በጥናት በደረሰባቸው የመንግሥት ሹመኞች፣ የመንግሥት ተቋማት ሰራተኞች፣ አቀባባዮችና ጉቦ ሰጪዎች ላይ ምርመራ እያደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

ነገር ግን ሙስና በባሕሪው በረቀቀ መንገድ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜም በሕጋዊነት ሽፋን የሚካሄድ በመሆኑ በመንግሥት ጥናት የተደረሰባቸው አካላትን ብቻ ለሕግ በማቅረብ የሚፈታ አይደለም ሲሉ በመግለጫቸው ጠቁመዋል።

መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ብሔራዊ ኮሚቴ ማቋቋሙን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

የብሔራዊ ከሚቴው አባላትም አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ ዶ/ር ጌዴዮን ጢሞቴዎስ፣ አቶ ተክለ ወልድ አጥናፉ፣ አቶ ሰሎሞን ሶቃ፣ አቶ ደበሌ ቃበታ፣ ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ እና አቶ አብዱሃሚድ መሃመድ መሆናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡

የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴው ውጤታማ እንዲሆን የሕብረተሰቡ ሙሉ ትብብር አስፈላጊ ነው፡፡ ሙስና በዋናነት የሚጠፋው ሕዝብ አምርሮ ሲታገለው ነውና፤ መንግሥትም የሕዝቡን ተሳትፎ በእጅጉ ይፈልገዋል ብለዋል።

ሕብረተሰቡ የሙስና ተዋንያንን በተመለከተ ያለውን መረጃ፣ ከቂምና ከበቀል ነጻ በሆነ መንገድ፣ ለብሔራዊ ኮሚቴው በመላክ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ አቅርበዋል።

በመግለጫው እንደተመላከተው ብሄራዊ ኮሚቴው የሚወስዳቸው እርምጃዎችና የእንቅስቃሴው ውጤት በየጊዜው ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል። የየክልሉ ርዕሳነ መስተዳድሮች በየደረጃው የሚሠሩ ክልላዊ ኮሚቴዎችን በቅርቡ እንደሚያቋቁሙም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡

# ስአፋር ክልል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በድህረ ጦርነት ማገገሚያ ዕቅዱ መሰረት በክልሉ ጉዳት የደረሰባቸውን መሰረተ ልማቶች ለመገንባትና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማከናወን ጥረት እንደሚደረግ ሚኒስትሯ አስታውቀዋል።

ድጋፉን የተቀበሉት የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ሃጂ አወል አርባ በበኩላቸው፤ በከተሞች ያለውን አሳሳቢ ድህነት ለማቃለል ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ እያከናወነ ያለውን ድጋፍ አድንቀው፤ ክልሉ የቀረበው ድጋፍ ለተፈለገው ዓላማ እንዲደርስ አስፈላጊውን ድጋፍ በቀጣይ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል።

የሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች በአፋር ክልል ከዚህ ቀደም ሲተገበሩ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ በክልሉ የመጀመሪያ የሆነውን በከተማ ደረጃ የሚተገበር ፕሮጀክት የበርካቶችን ሕይወት እያቃና መሆኑን ተናግረዋል።

አፋር ክልል በከተሞች አካባቢ እየተከናወነ ካለው ስራ በተጨማሪ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ጠቁመው፤ የደረሰውን ውድመት መልሶ ለመገንባት የሚረዳ ሰፊ ጥረት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የአፋር ክልል የክልሉን ነዋሪዎች ሕይወት ለማሻሻል የሚረዱ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለማሻሻል ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ የገለጹት ሃጂ አወል አርባ፤ በቀጣይ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ አስፈላጊው ድጋፍ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ በአፋር ክልል በተለያየ ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ ማቋቋም ሥራ ላይ የሚውል ድጋፍ እያቀረበ ይገኛል።

# “የቴሌኮም

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሆን ያደርገዋል።

እንዲህ አይነት ስራዎች፤ የእውቀት ሽግግር ይፈጥራል፣ የባንክ ዘርፉንና ኢኮኖሚውን ያሳድጋል፣ የፋይናንስ ዘርፉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ያስችላል፣ ተወዳዳሪነትን በመፍጠር ዘርፉ እንዲያድግ አዎንታዊ ሚና ይጫወታል ነው ያሉት፡፡

የኢትዮ- ቴሌኮም 40 በመቶ ለውጭ ገበያ መቅረቡና በኢትዮጵያ ሰላም መስፈን ለዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮች መተማመኛ ይፈጥራል። ኩባንያዎች ከፍ ያለ የፍቃድ ክፍያ ከፍለው መንግሥት የሚጠብቀውን ኢንቨስትመንት ማሳካትም ይችላሉ ብለዋል።

የኢትዮ-ቴሌኮምን 40 በመቶ ለሽያጭ ሲቀርብ መንግሥት 60 በመቶውን ይይዛል። ከዚህም 5 በመቶውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለመሸጥ በመወሰኑ የኢትዮ-ቴሌኮም 55 በመቶ በመንግሥት የሚያዝ መሆኑን አስታውሰዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ትግበራው ኢትዮ-ቴሌኮም ከሌሎች ሀገራት ኩባንያዎች ጋር ተወዳዳሪ በመሆን ወደ ሌሎች አገራትም ገበያ እንዲገባ እድል ይፈጥርለታል፡፡ በኢትዮጵያ ሶስት የቴሌኮም ኩባንያዎች መኖራቸው የሀገሪቱን አጠቃላይ እድገትም ከፍ ያደርገዋል።

በዓለም አቀፍ ጨረታ ኢትዮ-ቴሌኮምን የ40 በመቶ ሽያጭ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝና የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ ምቹ ሁኔታ ስላልነበረ መቋረጡን አስታውሰው፤ የኢትዮ ቴሌኮም እያደገ መምጣትና የሀገሪቱ ሰላም ለኢንቨስተሮች ምቹ በመሆኑ ውሳኔው የሚደገፍ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

መንግሥት የቴሌኮም ዘርፉን ለውጭ ገበያ ክፍት ለማድረግ ከወሰነ ሶስት ዓመት እንደሆነው፣ ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት በኢትዮጵያ ቴሌኮም ታሪክ ከ126 ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የውጭ ኩባንያዎች ግቡ ተብሎ ሳፋሪኮም ኩባንያ ጨረታውን አሸንፎ ገበያውን መቀላቀሉንም አንስተዋል።

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ አንድ ሚሊዮን ደንበኛ ማግኘቱን አስታውቋል ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ ይሄ የሚያሳየው የቴሊኮም ዘርፉ የኢኮኖሚ ዘርፉን የማሳደግ እድል እንዳለው ነው ብለዋል፡፡ አንድ ኩባንያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሄን ያህል ስኬት ማግኘቱ ትልቅ ውጤት አለው። ለቴሌኮም ተጠቃሚውም ምርጫ አግኝቷል፤ ምርጫ ሲኖር ደግሞ ውድድር አለ ሲሉም አብራርተዋል።

አቶ ዘመዴነህ እንደገለጹት፤ ኢትዮ ቴሌኮም ባለፉት ሶስት ዓመታት በቴሌኮም ሴክተር፣ በደንበኛ ቁጥር እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች እድገት ማምጣቱ ሊዘነጋ አይገባም። የዘርፉ ማደግ በባንክ ዘርፉ፣ በአይሲቲ ዘርፍና በአጠቃላይ ለሀገሪቷ ኢኮኖምሚ ጉልህ ሚና ይኖረዋልም ብለዋል።

የዛሬ ዓመት ተኩል መንግሥት በቴሌኮሙ ሁለት ፍቃድ ለመሸጥ አቅዶ ነበር። ለጨረታው ከተወዳደሩ ኩባንያዎች ውስጥ መንግሥት የመረጠው ሳፋሪኮምና የሥራ አጋሮቹ ለሚቀጥለው አስር ዓመት ከአስር ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት ስለሚያደርጉ ነው። ይህም ሁለተኛ ተወዳዳሪ የነበረው የደቡብ አፍሪካው ኤም ቲ ኤም ኩባንያን እንዳይመረጥ አድርጎታል ብለዋል።

አሁን እንደገና የቴሌኮም ጨረታ ሲወጣ ያልተመረጡ ኩባንያዎችን አዲስ እድል ይፈጥርላቸዋል። ባለፉት ሁለት ዓመታት ብዙ ችግሮች ነበሩ። አሁን ግን ለኢንቨስተሮቹ የሚያስተማምን ሰላም መጥቷል። ስለዚህ በሚቀጥለው ዓመትና ከዛ በኋላ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከ10 እስከ 11 በመቶ ያድጋል ብለው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይጠብቃሉ ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መሳው ሕዝባችን ለተጀመረው የጸረ- ሙስና ትግል ስኬት ንቁ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበታል!

ሙስና እለት እለት አቅሙ እያደገ ፤ የተጽእኖ አድማሱ እየሰፋ እንደ ሀገር ትልቅ ፈተና እየሆነብን ከመጣ አመታት ተቆጥረዋል። ይህንን ማህበራዊ ነቀርሳ ፈጥነን መቆጣጠር የሚያስችል አቅምና ቁርጠኝነት መፍጠር ካልቻልን የሀገርን ህልውና አደጋ ውስጥ ሊከት እንደሚችል ይታመናል።

ባለፉት 27 አመታት ከነበረው ሀገራዊ የፖለቲካ/ኢኮኖሚ ስርአት አኳያ ፤ ሙስና ልክ የሆነ ያህል በፖለቲካ መሪዎች ሳይቀር "ሌባ እስካልተያዘ ድረስ ሌብነት ስራ ነው" በሚል በአደባባይ ሳይቀር እንደ ስራ ተቀባይነት አግኝቶ እንደነበር የሚታወስ ነው። በዚህም እንደ ሀገር በነበርንበት ድህነት ላይ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" በመሆን ዜጎችን ብዙ ዋጋ አስከፍሏል።

በተለያዩ ወቅቶች በተለያየ መንገድ ችግሩን ለመቆጣጠር የተደረጉ ሙከራዎችም ቢሆን የፖለቲካ ስርዓቱ የችግሩ አካል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ከመፈክር፤ ትርጉም አልባ ከሆኑ ዘመቻዎች እና ዘመቻዎች ከፈጠሩት ትርምስምስ በዘለለ ያስገኘው ውጤት አልነበረውም።

ይህም በራሱ ሙስና በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ ከማድረግ ባሻገር አይነኬ መስሎ እንዲታይ የበለጠ አቅም አጎናጽፎታል። በማህበረሰቡ ውስጥም ሙሰኞች ከየጓዳ ወጥተው አደባባዮችን እንዲሞሉ ድፍረት ሆኗቸዋል። ከድፍረትም ባለፈ ሀገርን ወደ ማፍረስ መንገድ እንዲያመሩ የከፋ መታወር ውስጥ ከትቷቸዋል።

ህዝባችን በሄደበት፣ በደረሰበት ሁሉ ፤ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሸያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. የሚያጋጥሙት ሙሰኞች ከአቅሙና ከትግስቱ በላይ ሆነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ህዝባችን የከፈለው ሆነ እየከፈለው ያለው ዋጋ በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም፤ ህጋዊ መብቶቹን በገንዘብ ከመግዛት ጀምሮ፤ ሙሰኞች በሚፈጥሯቸው ግጭቶች እና ሁከቶች ሀብት ንብረቱን ጨምሮ ሕይወቱን ገብሯል።

ሕገ መንግስታዊ ስርአቱ ፤ ከስርአቱ የሚቀዱ ህጎች ሳይቀሩ በሙሰኞች አደጋ ውስጥ በመውደቃቸው የተነሳም፤ በአራቱም የሀገሪቱ ክፍሎች ዜጎች አላግባብ ለመፈናቀል፣ ለመሰደድ ከዛም አልፎ ተስፋ ቢስ ሆነው ሞትን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ተገድደዋል።

አሁን ሙስናን በተመለከተ በሀገራችን ያለው ተጨባጭ እውነታ ችግሩ የቱን ያህል እንደተስፋፋና እንደገነገነ ከማሳየት ባለፈ፤ የቱን ያህል ህዝባችን ነገ ላይ ተስፋ እያደረገ ላለው ብልፅግና ፅልመት ሆኑ ከፊት እንደቆመ ጭምር ያመላከተ ነው።

ከዚህም በላይ ትናንትናና ዛሬ ለሀገር ህልውና ተግዳሮት እንደሆነ ሁሉ ፤ ከፍ ባለ ሀገራዊ ቁርጠኝነት ተዋግተን ካላሸነፍነው ነገ ላይ ሀገርን እንደ ሀገር ሊያሳጣን የሚችል ከፉ ነቀርሳ እንደሚሆን በተጨባጭ ያሳየ ነው።

በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እንደ ሀገር ባጋጠሙን ፈተናዎች ምክንያት መንግስት በፀረ - ሙስና ትግሉ ላይ የነበረውን ትኩረት መቀነሱ ለሙሰኞቹ እንደ መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸው የብሄራዊ ፈተናው አካልና አቅም መሆን ችለዋል።

ይህን የሀገርን ህልውና ስጋት ውስጥ እስከ መክተት የደረሰውን የሙስና ጉዳይ በማያዳግም መንገድ በቅርጠኝነት ታግለን ማሸነፍ/ መቆጣጠር ካልቻልን ነገ ላይ የምናስበውንና ተስፋ ያደረግነውን ብልጽግና ቀርቶ ዛሬ ላይ እንደ ሀገር የቆምንበትን ሀገር መሰረት አናግቶ ማገር እንደማያሳጣን ማስተማመኛ አይኖርም።

ከዚህ አንጻር መንግስት ሙስናንና ሙሰኞችን ለመዋጋት በጥናት ላይ ተመስርቶ የጀመረው ዘመቻ የሚበረታታ፤ ሀገርን ከፍ ካለ ጥፋት የሚታደግ፤ የህዝባችንን ነገዎች ብሩህ ማድረግ የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል።

መላው ህዝባችንም የሙስና ጉዳይ በእለት ተእለት ሕይወታችን ላይ ከሚፈጥረው ተግዳሮት /ፈተና በላይ በብዙ ትውልዶች መስዋእትነት ዛሬ ላይ የደረሰችውን ሀገራችንን ህልውና ስጋት ውስጥ ሊከት እንደሚችል በሰከነ መንፈስ ሊረዳ ይገባል።

ዛሬ ላይ እንደ ሀገር እየተገዳደሩን ያሉ ችግሮች በአንድም ይሁን በሌላ የዚህ ማህበራዊ ነቀርሳ /ሙስና ውጤት መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ያስከፈሉን ዋጋ የቱን ያህል የከፋ እንደሆነ መላው ህዝባችን በተገቢው መንገድ በመረዳት በጸረ-ሙስና ትግሉ በንቃት መሳተፍ ይጠበቅበታል።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም" በሚል በማህበራዊ ገጻቸው ያስተላለፉት መልዕክት፤**

# የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም አስመልክቶ የተላለፈ መልዕክት

ሙስና ሀገርን የሚበላ ነቀዝ ነው። የሀገርን አንጡራ ሀብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ ነው። ዋልጌ ባለሥልጣናት፣ በፍቅረ ነዋይ የታወሩ ደላሎች እና ባለሃብቶች አንድ ላይ ሲገጥሙ፤ ከነዚህ የሌብነት ፈታውራሪዎች ጀርባ ብዛት ያላቸው ዜጎች መሰለፍ ሲጀምሩ ሙስና የተባለው ነቀዝ ሀገርን እንደ ወረርሽኝ ያጠቃታል።

ሙስና በየትኛው ቦታና በየትኛውም ዘመን ሊኖር ይችላል። ነገር ግን የሀገርን ልማት አጥንቱ ድረስ እስከ መጋጥ ከደረሰ ሙስና አንድ አደገኛ ወረርሽኝ ሆኗል ማለት ነው። ሙስና ሀገርን ሊያፈርስ የሚችል የደኅንነት ሥጋት መሆኑን ያስመሰከሩ ሀገሮችን በዘመናችን አይተናል። የአደንዛዥ ዕጽ፣ የኮንትሮባንድ፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ፣ የንግድ ማጭበርበር ሙስናን ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ይፈልጉታል።

በዓለማችን የተጀመሩ ጦርነቶች እንዳይጠናቀቁ፤ ግጭቶች እንዳይበርዱ፣ ሕዝቦች እርስ በእርስ እንዲጋጩ፣ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ሙሰኞች ከዚህ አይነት ቀውሶች ስለሚያተርፉ ነው። ሙስና ዛሬ የሀገራችን የደኅንነት ሥጋት ሆኗል። ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻችን እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው።

የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌሊት እየሠራ ነው። ሕዝባችን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሽያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው። በተለያዩ ጊዜያት ከሕዝብ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ከጸጥታ ሥጋቶች እኩል ሙስና የብልጽግና ጉዟችን ዋናው ዕንቅፋት መሆኑን አንስቷል።

መንግሥት በየደረጃው የሚገኘውን መዋቅር በመፈተሽ፣ አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ ሥራዎችን እያሳለጠ ሥራዎችን ከእጅ ንክኪ ነጻ በማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ አመራሮችንና ሌሎች ተዋንያንን ለሕግ በማቅረብ፣ ሙስና ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠርለት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

ነገር ግን ሀገራችን ያጋጠማትን ጦርነትና ኮሮናን የመሳሰሉ ወረርሽኞች የመንግሥትን ትኩረት ወስደዋል ብለው ያሰቡ ሙሰኞች፣ በየቦታው ተሰግስገውና ኔት ወርክ ዘርግተው፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት እየሠሩ መሆናቸውን በዝርዝር የቀረበው የጥናት ሪፖርት ያሳያል።

መንግሥት በጸጥታው ዘርፍ እንዳደረገው ሁሉ በሙስና ላይ ጠንካራና የማያዳግም ኦፐሬሽን ማድረግ እንዳለበት የጥናቱ ውጤትና የሕዝብ ውይይቱ ግምገማ ያመለክታል። በአንድ በኩል የመንግሥት ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ለሙስና ያላቸውን ተጋላጭነት የማጥፋት ሥራ ይሠራል። በሌላ በኩል ደግሞ የሙስና ተዋንያንን የማጋለጥና በሕግ የመጠየቅ ተግባር ይከናወናል።

መንግሥት በጥናት በደረሰባቸው የመንግሥት ሹመኞች፣ የመንግስት ተቋማት ሰራተኞች፣ አቀባባዮችና ጉቦ ሰጪዎች ላይ ምርመራ እያደረገ ይገኛል። ነገር ግን ሙስና በባሕርዩ በረቀቀ መንገድ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜም በሕጋዊነት ሽፋን የሚካሄድ በመሆኑ በመንግሥት ጥናት የተደረሰባቸው አካላትን ብቻ ለሕግ በማቅረብ የሚፈታ አይደለም።

ሙስናን ከሥር ከመሠረቱ ለመንቀል እንዲቻል ከሕግና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ የሙስና ተዋንያን ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ እርምጃ ያስፈልጋል።መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሟል።

ብሔራዊ ኮሚቴው ሰባት አባላት ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም፡-

1. አቶ ተመስገን ጥሩነህ
2. ዶ/ር ጌዴዎን ጢሞቴዎስ
3. አቶ ተክለ ወልድ አጥናፉ
4. አቶ ሰሎሞን ሶቃ
5. አቶ ደበሌ ቃበታ
6. ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ
7. አቶ አብዱሃሚድ መሃመድ ናቸው።

ይህ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣትና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት እንዲችል የኅብረተሰቡ ሙሉ ትብብር እጅግ አስፈላጊ ነው። ኅብረተሰቡ በሙስና ላይ በሚደረገው ዘመቻ ሊሳተፍ እንደሚገባ በተለያዩ መድረኮች ሲያነሣ ቆይቷል። መንግሥትም ይሄንን የሕዝብ ተሳትፎ በእጅጉ ይፈልገዋል፤ ምክንያቱም ሙስና በዋናነት የሚጠፋው ሕዝብ አምርሮ ሲታገለው ነውና።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ የሙስና ተዋንያንን በተመለከተ ያለውን መረጃ፣ ከቂምና ከበቀል ነጻ በሆነ መንገድ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አድራሻዎች ለብሔራዊ ኮሚቴው በመላክ ሙስናን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ እናቀርባለን።

የሚቀርቡ ጥቆማዎች የጠቋሚዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥንቃቄ እና ሚስጥራዊነት በጠበቀ መንገድ ተይዘው ይመረመራሉ። ብሄራዊ ኮሚቴው የሚወስዳቸው እርምጃዎች እና የእንቅስቃሴው ውጤት በየጊዜው ለህዝብ ይፋ ይደረጋል። የየክልሉ ርእሳነ መስተዳድሮች በየደረጃው የሚሠሩ ክልላዊ ኮሚቴዎችን በቅርቡ እንደሚያቋቁሙ በዚሁ አጋጣሚ እንገልፃለን።

* ስልክ ቁጥር፡ 9555
* አጭር የፅሁፍ መልዕክት : 9555
* ድረ ገፅ ፡ http://www.9555pmo.et/
* ኢሜይል : http://9555pmo.et/
*ቴሌግራም : https://t.me/PMOfeedback

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ባህላዊ ወረቶቻችንን ለዘላቂ ሰላም

ሰሞኑን በእጄ የገባውን የታዋቂዊ አሜሪካዊ የፖለቲካ ሳይንቲስት ፍራንሲስ ፉኩያማን በባህላዊ ወረት/Cultural Capital/ላይ በጥልቀት ትንታኔ የሚያደርግና ሞጋች ማለፊያ መጽሐፍ ፤ "The Great Disruption እያነበብሁ፤ በዚሁ ጋዜጣ ባህላዊ ወረቶቻችን በአግባቡ ስራ ላይ ከዋሉ ለእርቅ፣ ለመደመርና ለሀገራዊ ምክክር ያላቸውን ፋይዳ ያመላከትሁባቸውን መጣጥፎች አስታውሼ የሰሞኑን የሰላም ስምምነት ለማዝለቅ ያላቸውን የማይተካ ፋይዳ ለማነሳሳት ጉድ ጉድ ስል ፤ ዛሬም የባህላዊ ወረቶቻችን እንጥፍጣፊ ከኢትዮጵያዊነት ጽዋ ጨርሶ አለመድረቁን አረጋገጥሁ። ቀደም ሲልም በተለያዩ እጅን በአፍ በሚያስጭኑ ሰናይ ተግባራት ዛሬም አብሮነታችን ከኅሳ፣ ከሃይማኖትና ከሌላ ማንነት በላይ መሆኑን አረጋግጠውልኝ ተስፋየን ሲያለመልሙት ቢባጁም ሰሞነኛው ክስተት ግን የተለየ ነው። ምንም እንኳ ሚዲያዎቻችን ባላየ ባልሰማ ቢያልፉትም።

ሰሞኑን ኮሜዲያን እሸቱ መለሰ በካሊፎርኒያ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለሚገነባ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎት የሚሰጥ ተቋም እርስት መግዣ በዩቲውብ በቀጥታ ስርጭት 1 ሚሊየን ዶላር ለማሰባሰብ ሲነሳ ኢትዮጵያውያን ከሀገር ቤትና ከመላው ዓለም ኦርቶዶክስ፣ እስላም፣ ፕሮቴስታንትና ዋቄ ፈና ሳይሉ፤ አማራ ፣ ትግሬ ፣ ኦሮሞ፣ አፋር ፣ ሶማሌና ሌላ ሳይሉ ፤ ሀብታምና ድሀ ሳይሉ፤ ከአረብ ሀገር የቤት ሰራተኛ እስከ ተሳካለት ዲያስፖራ ፤ ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ ሳይሉ በመረባረብ አሳክተውታል። ይህ ዛሬም ከጥንት ሲወራረሱ የመጡ ባህላዊ ወረቶቻችን ተዳፈኑ እንጂ አልጠፉም ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር የሚያስደፍር ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ኮሜዲያን እሸቱ የባህላዊ ወረቶቻችንን ዕምቅ አቅም ገላልጦ አሳይቶናል። በዚህ ላይ መጨመር የሀገሬው ኃላፊነት ነው።

ባለፉት ሁለት አመታትም ሆነ ከዚያ በፊት በሀገራችን የሆነውን ሰቆቃና ግፍ መለስ ብሎ አስታውሶ የሰሞኑን የኮሜዲያን እሸቱን አርዓያነት ያለው ተግባር በአንክሮ ላስተዋለ ኢትዮጵያ እውነትም ቅኔ ፣ ሰምና ወርቅ ናት ቢል አልተሳሳተም። ኢትዮጵያዊነት ከየትኛውም ማንነት በላይ መሆኑን ኮሜዲያን እሸቱና በሰሞኑን ሰናይ ተግባር የተሳተፉ መላ ኢትዮጵያውያን እማኝ ናቸው። ዳሩ ግን ባለፉት ጥቂት አመታትም ሆነ ከዚያ በፊት አንገታችንን የሚያስደፉ የጭካኔና የግፍ ጥጎችን ታዝበናል። እዚህ ማህበራዊ ቀውስና ስብራት ላይ የደረስነው ግን በአንድ ጀንበር አይደለም። ቢያንስ ላለፉት 50 አመታት ባህላዊ ወረቶቻችን በመሸርሸራቸው ነው እዚህ ላይ የደረስነው።

በነገራችን ላይ ከፍ ብዬ በጠቀስሁት የፉኩያማ መጽሐፍ የሰው ልጅ አኩሪ ወጉንና ባህሉን እያጣ የመጣው ከኢንዱስትሪ አብዮት ማግስት ጀምሮ ነው። በዚህ ተጽዕኖ ያልተነካ ሀገር የለም። መተማን ፣ መተሳሰብ ፣ መረዳዳት ፤ ትዳር መያዝ ቤተሰብ መመስረት እየተቀዛቀዘ ፤ ፍቺ እየተበራከተ፤ ልጆች ከጋብቻ ውጭ እየተወለዱ፤ ዕምነትንና ሃይማኖትን ማጥበቅ እንደ ኋላቀርነት እየተቆጠረ፤ የበይነ መረብ መፈጠርን ተከትሎ ልጅ ከወላጅ ፣ ሚስት ከባል እየተራራቁ ፤ በብቸኝነትና በጭንቀት ትውልድ እየተሰቃየ ፤ ትውልዱ ለልቅ ወሲብና ሌላ ሱስ እየተጋለጠ ይገኛል ።

ሕዝብ በመንግስት ተቋማት ላይ እምነት እያጣ ፤ ግለሰብ ለግለሰብ አልተማመን እያለ መሆኑን በዚሁ መጽሐፍ በመረጃ ተደግፎ በስፋት ተተንትኗል። ከ70 አመታት በፊት በመንግስት ተቋማት ላይ አሜሪካውያን የነበራቸው ዕምነት 70ና80 በመቶ ይደርስ ነበር። ዛሬ ላይ ግን ወደ 20ና 30 በመቶ አሽቆልቁሏል። ዛሬ ላይ ከመራጩ ግማሹ በተለይ የትራምፕ ደጋፊ የ2020 ምርጫ ተጭበርብሯል ብሎ የሚያምን ነው። ከአራት አሜሪካውያን ሶስቱ የአሜሪካ መደበኛ ሚዲያዎችን አያምኑም።

በሀገራችን ያለውን ሁኔታ ለመግለጽ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ዜጎች በመንግስት ተቋማት ላይ የነበራቸው ዕምነት ከአንዳንዶች በስተቀር እየተሸረሸረ መሆኑን ለመናገር ሞራ ገላጭ መሆንን አይጠይቅም። ዛሬ በሀገራችን እየተስተዋሉ ያሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባህላዊ ወረቶቻችን ኪሳራ ጋር የሚያያዙ ናቸው። የሀገር ሕዳሴም ሆነ ብልጽግና ያለ ባህላዊ ወረቶቻችን ህዳሴና ትንሳኤ እውን ሊሆን አይችልምና በዚህ ረገድ ብዙ ስራ ይጠበቅብናል። የግብረ ገብ ትምህርት መጀመሩ፤ ስርዓተ ትምህርቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች፤ በሃይማኖት ተቋማት ተሓድሶና አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ውጤት ካልታገዘ መጭው ዘመን ከዚህ የከፋ እንደሚሆን ልብ ማለት ያሻል።

ሰሞኑን በፕሪቶሪያ ደቡብ አፍሪካ በሕወሓትና በኢፌዴሪ መንግስት በቀድሞዎቹ የናይጀሪያና የኬኒያ ፕሬዝዳንቶች አደራዳሪነት ስለተደረሰው የሰላም ስምምነት ሳብሰለስል፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በተለይም ላለፉት ሁለት አመታት በሰሜን የሀገሪቱ ክፍል የተካሄደውን ጦርነት ጨምሮ የተለያዩ ጽንፈኛ ሀይሎች የፈጸሟቸውን ለጆሮ የሚቀፉ፣ ለመስማት የሚከብዱ ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን እና ነውሮችን እያሰብኩ ነው ። በየተቋማት የተንሰራፋውን ብልሹ አሰራርና ሙስና፤ የግብይት ስርዓቱ መገለጫ እየሆነ የመጣውን ገፈፋ ፤ በንግዱ ማህበረሰቡ እየተስተዋለ ያለውን ስግብግብነትና አልጠግብ ባይነትና የስነ ምግባር ችግር ባስተዋልሁ ቁጥር ሀገር በተቋምና በሕግ ብቻ እንደማይቆም እያረጋገጥሁ ነው።

ከገባንበት ሁለንተናዊ ቀውስ ለማገገምም ሆነ በሀገራችን ዘላቂ ሰላምና አንድነት ለማረጋገጥ የጣልናቸውንና የረሳናቸውን ባህላዊ ወረቶች እንዲያንሰራሩና መልሰው እንዲያቋጠቅጡ ሌት ተቀን መስራት ይጠበቅብናል። ይህን ማድረግ ካልቻልን ብልጽግናችን ሙሉ ሊሆን አይችልም። ለመሆኑ ለሀገራችንና ለተቋማት ስራ አካላት ጤንነት የልብ ትርታ የሆነው ባህላዊ ወረት ምንድን ነው፤

ከዚያ በፊት ባህል ፣ ባህላዊ ወረትስ ምንድን ነው የሚለውን ለመግባቢያ ያህል እንመለከታለን። ባህል ሁሉንም የሚያስማማ የሚያግባባ ወጥ የሆነ ትርጉም ብያኔ ባይኖረውም የአንድ ማህብረሰብ ወይም ሕዝብ ዕምነት፣ ልማድ ፣ ወግ በኪነ ጥበብ እና በስነ ጥበብ ተዳውሮ ፣ ተሸምኖ ፣ ተንሰላስሎ የመገኘት፣ የመገለጥ ኽጉርጉር ሕብራዊ ቀለም ነው። በደስታ፣ በሀዘን፣ በስራ፣ በሃይማኖት፣ በትምህርት ፣ ወዘተ . የሕይወት አንጓዎች ይገለጻል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ባህልን፡- የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት፣ ...። በማለት ሲተረጉመው።

የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በበኩሉ ባህል፡- ልማድ ፣ ደንብ ሲል ይፈታዋል። የእንግሊዘኛው ሜሪያም ዌብስተር መዝገበ ቃላት በበኩሉ ዘርዘር አድርጎ ይተረጉመዋል። ይበልጥ ግልፅ እንዲሆንና የትርጓሜውን ስፋት ለመገንዘብ እንዲረዳ በመገኛ ቋንቋው እንዳለ አስቀምጨዋለሁ።

culture: the beliefs, customs, arts, etc., of a particular society, group, place, or time: a particular society that has its own beliefs, ways of life, art, etc.: a way of thinking, behaving, or working that exists in a place or organization (such as a business)

1 . Cultivation, tillage

2 . The act of developing the intellectual and moral faculties especially by education

3 . Expert care and training <beauty culture>

4 a . Enlightenment and excellence of taste acquired by intellectual and aesthetic training

b . Acquaintance with and taste in fine arts, humanities, and broad aspects of science as distinguished from vocational and technical skills ,

ባህላዊ ወረት ( Cultural capital ) የሚለው ሀረግ ፔሬ ቦርዴው በተባለ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የተነሳ የስነ ሕብረተሰብ ተመራማሪ እንደተፈጠረ የተለያዩ የዘርፉ ድርሳናት ያትታሉ። ባህላዊ ንብረት በማህበረሰብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት ቦታ ከፍ ለማድረግ ዕውቀትን፣ ፀባይና ክህሎትን የማሳደግ የማካበት ሂደት ነው። ባህላዊ ንብረት በግለሰብ፣ በማህበረሰብ ከፍ ሲልም በሕዝብ በሀገር ይሰላል። የበለፀገ ባህላዊ ንብረት ያካበተ ግለሰብ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ከፍ እንደሚያደርገው ሁሉ ያደገ የለማ ባህላዊ ንብረት ያለው ማህበረሰብ ሕዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ ያለ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ባህል ማለትም የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ ፣ ልማድ፣ እምነት ፣ ወዘተ . በሂደት በዕውቀትና በክህሎት እየበለፀገ፣ እየዳበረ ሲሄድ ለሀገር ሰላም ፣ አንድነት ከፍ ሲልም እድገት የላቀ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተቃራኒው ባህል በዕውቀት ፣ በክህሎት ካልበለፀገ አይደለም ለሀገር ሰላምና ዕድገት መዋል ይቅርና የማህበረሰቡን እሴቶች ጠብቆ ማቆየት ካለማስቻሉ ባሻገር የዕለት ተዕለት ችግሮችን እንኳ መፍታት የሚሳነው ይሆናል። ባህላዊ ወረት እንደ ኢኮኖሚያዊ ወረት ማለትም ገንዘብ በአግባቡ ኢንቨስት ተደርጎ ሰላምን፣ ፍቅርን ፣ እርቅን ፣ መነጋገርን፣ መቀባበልን ፣ መከባበርን ፣ መተባበርን ፣ አንድነትን፣ ወዘተ . እውን ማድረግ ካልቻለ እንደባከነ እንደከሰረ ሊቆጠር ይችላል።

ሀገርን ሕዝብን ከግጭት ፣ ከቀውስ ፣ ከመፈናቀል፣ ከመጠራጠር ፣ ከጥላቻ ፣ ከበቀል ፣ ወዘተ . መታደግ አልቻለማ። እስኪ ለአንድ አፍታ ባህሎቻችንን እምነቶቻችንን ወይም ባህላዊ ወረቶቻችንን ከዚህ አኳይ እንመዝናቸው። ባክነዋል ወይስ በአግባቡ ስራ ላይ ውለዋል ! ? አሁን ከምንገኝበት ሀገራዊ ቁመና አንጻር ባክነዋል ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል። ታዲያ እነዚህን ባህላዊ ወረቶቻችንን እንደ ጦር ዕቃ ለብሶ እንደ ጥሩር ደፍቶ መውጣት መግባት ፣ መመላለስ ለምን ተሳነን ! ? መልሱ ቀላል ነው። ላይ ላዩን እንከውናቸዋለን እንጂ አንኖራቸውም።

በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም። "ባለንጀራህን ፣ ጎረቤትህን እንደ ራሳህ ውደድ "የሚሉ አብርሀማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን ፣ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን ! ? በአንድ አምላክ በዋቄ ፈና እያመን ኢ ሬቻን በየአመቱ እያከበርን እየከወን ይቅር መባባል ለምን ተሳነን !? መልሱን ለማግኘት ሚስጥሩን ለማወቅ ሞራ ማስገለጥ ወይም ኮከብ ማስቆጠር አያሻም። መልሱ ቀላል ነው ። እሱም ባህላዊ ወረቶቻችንን በካዘና ቆልፈን አስቀመጥን እንጂ ስራ ላይ ስላላወልናቸው ( ኢንቨስት ) ስላላደረግናቸው ነው። የሰላም ስምምነቱን ሆነ ሀገራዊ ሰላምና አንድነት በዘላቂነት እውን ለማድረግ የተቆለፈባቸውን ባህላዊ ንብረቶች ከካዘና አውጥቶ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ በፍጥነት ማፍሰስ ኢንቨስት ማድረግ ይጠይቃል ።

በኢኮኖሚክስ አስተምህሮ ባህል ከተፈጥሮ ፣ ከሰውና ከአካላዊ ፣ ቁስ አካላዊ ( physical ) ቀጥሎ 4ኛው ንብረት ሆኖ መጠናት ፣ መተንተን ከጀመረ ከራርሟል ። በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሀገር ዕድገትና ለዘላቂ ሰላም አስተዋጾ ያበረክታል ። ሰላም በሌለበት ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም ሆነ ብልፅግና ሊታሰብ አይችልምና። ለሀገር ግንባታ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ወሳኝ ሚና ከሚጫወተው ፓለቲካዊና አስተዳደራዊ ስርዓት በተጨማሪ ለዘመናት እንደ ሕዝብ ፣ እንደሀገር አጋምዶ ያቆየን ባህላዊ ወረታችን ነው ።

ሁነቱን ፣ ክዋኔውን ፣ መንፈሱን ጠብቆ ተንከባክቦና አልምቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ፣ ማስቀጠል፣ ማክበርና ማስተዋወቅ ትልቅ ኃላፊነትም አደራም ነው። ሆኖም የመጨረሻ ግብ ሆኖ ግን ሊወሰድ አይገባም። ቱባነቱን እንደጠበቀ ማደግ ዘመንና ትውልድ መዋጀት ይጠበቅበታል። አዎ ! የትውልዱንና የዘመኑን ህፀፅ የሚያርም ለምፅ የሚያነጻ ፣ የሚዋጅ መሆን አለበት ። ዘረኝነትን ፣ ጥላቻን ፣ ቂም በቀልን፣ ደባን ፣ መከፋፈልን ፣ ወዘተ . መቤዥ ፣ መዋጀት አለበት ።

ባህላዊ ወረታችንን ይበልጥ በማጎልበት ፣ በማልማትና በማስፋት ለመጻኢ እድላችን ፣ ለነገ ተስፋችን ፣ ለእርቅ ፣ ለሰላም ፣ ለአንድነት ፣ ለሁለንተናዊ ብልፅግና ፣ ወዘተ . ልናውለው ይገባል። ስኬቶቻችንን የምናወድስበት ፣ ፈተናዎቻችንን የምንሻገርበት ነገአችንን የምንተልምበት ጭምር አድርጎ ስለመጠቀም አብክረን ማሰብ ያስፈልጋል። የፍቅር ፣ የእርቅ፣ የሰላም ፣ የአብሮነት፣ የማካፈል ፣ የመተባበር ፣ የመተጋገዝ ፣ የመረዳዳት ፣ የምስጋና፣ ወዘተ . ባህሎች ፣ ልማዶች ፣ ዕምነቶች፣ ሀይማኖቶች ከፍ ሲልም ድምር ባህላዊ ወረቶች ባለቤት እንዲሁም የጥንታዊት ሀገር ባለቤት ሆነን አንድነትን በመከፋፈል ከሰዋን ፣ ፍቅር ከጎደለን፣ እርቅ ከገፋን ፣ ሰላም ከራቀን፣ አብሮነትን በቀዬአዊት ከተካን፣ ማካፈልን በስስት ከቀየርን፣ መተባበርን በመለያየት ከለወጥን፣ ምስጋናን በእርግማን ከተካን ፣ ወዘተ . ምኑን ሙሉኡ ሆነው !?።

ባለፉት ሶስትና አራት አመታት ያለፍንባቸው ሀገራዊ ውጣ ውረዶች ፣ አሳፋሪ ድርጊቶች እውነት የእነዚህ ሁሉ መንፈሳዊና ባህላዊ ፀጋዎች ባለቤት ስለመሆናችን የሚመሰክሩ ናቸው !? እስኪ ሌሎችን አቆይተን ከአዲሱ አመት ወዲህ እንዲሁም ወደፊት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚከበሩ መንፈሳዊና ባህላዊ ሁነቶች የተሸከሙትን ግዙፍ መልዕክቶችና አንድምታዎች አለፍ አለፍ ብለን እየተመለከትን ሒሳብ እናወራርድ።

ፍቼ ጨምበለላ ፣ ቡሔ ፣ ሻደይ ፣ አሸንዳ ፣ ሶለል አይነ ዋሬ ፣ እንቁጣጣሽ ፣ መስቀል ፣ መስቀላዮ ፣ አጋመ፣ ጊፋታ ፣ ኢ ሬቻን ፣ ጋሮ ፣ ቺሜሪ ፣ ወዘተ . በአንድም በሌላ በኩል በተለያዩ የሀገራችን ማህበረሰቦች የሚከበሩ ሀይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ክዋኔዎች ናቸው ። ሁሉም ማለት ይቻላል ተስፋን ፣ ፍቅርን ፣ ነፃነትን ፣ አብሮነትን፣ ምስጋናን ፣ እርቅን፣ ይቅርታን ፣ ወዘተ . የሚያውጁ፣ የሚለፍፉ ናቸው ። ግን በነቂስ ወጥተን ለዘመናት በየአመቱ በአደባባይ የምናከብራቸው የምንዘክራቸውን ያህል በዕለት ተዕለት ኑሮአችን አንኖራቸውም ። አንለማመዳቸውም።

ይሁንና ከገጠሙን ቀውሶች ፣ ፈተናዎች መውጣት ማገገምና ማንሰራራት የቻልነው በቀሩን ሽርፍራፊ እንጥፍጣፊ በባህላዊ ንብረቶቻችን መሆኑን ልብ ይሏል ። በተለይ ባለፉት 30 አመታት ቀን ከሌት እንደ ተሰበከው ልዩነት ፣ ጥላቻና ዘረኝነት ቢሆን ኑሮ እርስ በእርስ ተበላልተናል ። ተጨራርሰናል። ለዚህ ነው መዳኛችን ፣ ማገገሚያችንና ማንሰራሪያችን የሆነውን ባህላዊ ወረት ወደሙላቱ መመለስ ለነገ የሚባል ጉዳይ የማይሆነው ። ባህላዊ ንብረታችን ለበጎ አላማ ሲውል ሀገርን ከጥፋት ከእልቂት እሳት እንደሚታደግ በጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች ተመልክተናል ።

የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ለበቀል ተነስቶ የነበረውን የአርባ ምንጭና የአካባቢውን ወጣት ለምለም ሳር ይዘው ተንበርክከው በመለመን ቁጣውን አብርደው መልሰውታል። ይህን የሀገር ሽማግሌዎች ገድል በጥሞና ለተረዳው የአርባ ምንጩን እሳት ብቻ አይደለም ያጠፉት የአርባ ምንጩን ጥፋት ተከትሎ በመላ ሀገሪቱ ሊዛመት የነበረውን የበቀል ሰደድ እሳት ጭምር እንጅ ። ቁጣ አብራጁ ይህ የጋም አባቶች ልመና ( ጋሞ ወጋ ) እየጠፋ ፣ ትኩረት እየተነፈገው ያለው ባህላዊ ንብረታችን ተጠብቆ ለትውልድ ሲተላለፍ ሀገርን እንዴት ማዳን እንደሚችል ጥሩ ማሳያ ነው ። የጋሞ አባቶች የ2011 ዓ.ም ልዩ የበጎ ሰው ተሸላሚ መሆናቸው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለ አንዳንች ልዩነት ዳር እስከዳር አድናቆትን ተቀባይነትን ያተረፈው በዚህ እሳቤ ነው ።

ሰላምን ፣ ፍቅርን ፣ ይቅርታን ለማነፅ ፣ ለመገንባት ከምንሰጠው ትኩረት ባልተናነሰ በየአካባቢው እንደ ጋሞ ወጋ አይነት የሽምግልና ፣ የእርቅ ባህላዊ ካፒታሎቻችንን ላይም መስራት ይጠበቅብናል ። ከዚህ መሳ ለመሳ የአክራሪነት አዝማሚያ ፣ እኩይ አስተሳሰብ እንዲገታ ብሎም ተሸንፎ ከሰላምና ከእርቅ መንገድ ገለል ፣ ዘወር እንዲል ድልብ የሆኑ ባህላዊ ወረቶቻችን ጥንስስ ፣ እርሾ የማይተካ ሚና አላቸው። ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህላዊ ንብረቶች ባለፀጋ ስለሆኑ የየራሳቸውን መዋጮ ማበርከትና ወደ ስራ መግባት ይጠበቅባቸዋል።

በየአካባቢያችን ፣ በየቀዬአችን የምናንፀው ፣ የምናቀነቅነው ከባቢያዊ ብሔርተኝነት ወደ አክራሪነት ፣ ፅንፈኝነት የሚያንደረድር ወደገደል አፋፍ የሚገፉ ስለሆነ እነዚህን ባህላዊ ወረቶች በመጠቀም መግታት ያስፈልጋል ። የዜጎች ማንነት እሴት እንደተከበረ ወደ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚያደርሰንን ቀና መንገድ በቅንነት መቀላቀል ፣ መያያዝ ይገባል። ይህ ሀገራዊ ብሔርተኝነትም ከገደቡ ፣ ከውሃ ልኩ እንዳያልፍ ጥንቃቄ ማድረጉ እንዳለ ሆኖ ። አይደለም ዘውጌአዊ፣ ወንዜአዊ ብሔርተኝነት ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት በአግባቡ ካልተያዘ ፤ የጎረቤቱን የሚጎመጅ ፣ የሚመኝ ፣ የሚመቀኝ ሆኖ የመውጣት አደጋ ስላለው በብልሀት ፣ በማስተዋል ሊቀነቀን ይገባል። በዛድባሬ ይመራ የነበረው " የታላቋ ሶማሊያ " አክራሪ ብሔርተኝነት ለዚህ ጥሩ አብነት ነው ።

ባህላዊ ወረቶቻችንን መልሰን እናልማ !

# “ይድረስ ለኢትዮጵያዊያን”

## ረ/ፕ አደም ካሚል ፋሪስ

ግርማ መንግሥቴ

(ካለፈው የቀጠለ)

እንግዳችን፣ ደጋግመን እንደምንናገረው፣ ለሚዲያ አዲስ አይደሉም። የዚህን ጽሑፍ ቀዳሚ ክፍል ባለፈው ሳምንት ስናቀርብ ሰፋ አድርገን እንዳብራራነው ለሚዲያ ቅርብ ብቻ ሳይሆኑ፣ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተገደቡ ሰው አይደሉም። በመሆኑም በአገራቸው ጉዳይ በተገኘው ርእሰ ጉዳይ ላይ ገንቢ አስተያየት ከመስጠት አይቆጠቡም። የተጣመመውን ከማቃናት፤ የጎበጠውን ከማቅናት፤ የሳተውን ከማስተካከል .... ወደ ኋላ ያሉበትን ጊዜ ማስታወስ ይከብዳል። በተለይም ኢትዮጵያን በተመለከተ ተናገረው አይጠግቡም።

የታሪክ ተመራማሪና ጸሃፊው ረ/ፕ አደም ካሚል ፋሪስ በተለይ በኢትዮ-አረብ ጉዳይ ላይ ተራቅቀውበታል። ኃይማኖታዊ አስተምህሮን ዘልቀውታል፤ የዓባይና ያስከተለውን ስልጣኔ በተመለከተ ከበቂ በላይ ፈትሸውታል፤ የሰላጤው አገራትን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ቃኝተዋል። ”በኢትዮ-አረቡና አካባቢው ምን ቀራቸው?” ከተባለ መልሱ ”ምንም።” ነው። በፓን አፍሪካኒዝም እሳቤም ዙርያ በርካታ መጽሃፍትን አገላብጠዋል።

ባለፈው ሳምንትም ኢትዮጵያ በርካታ የተፈጥሮ ሃብት ያላት፤ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ መስህቦች የታደለችና ተስማሚ አየር ጻባይ ያላት ውብ አገር ናት። ስለዚህም ኢትዮጵያ ላይ ተቀምጦ ተራብኩ ማለት ወንዝ ላይ ተቀምጦ ውሃ ጠማን እንደማለት ነው ሲሉ ሃሳባቸውን አጋርተውናል። የዛሬውንና የመጨረሻውን ደግሞ እነሆ ይዘን ቀርበናል።

ረ/ፕ አደም ካሚል የዛሬውን ሀሳባቸውን የሚጀምሩት ባለፈው ካቆሙበት ሲሆን፣ እሱም የኢትዮጵያ በዓባይ ግድብ የተጠቃሚነት መብትን የሚመለከተው ነው።

ኢትዮጵያ 85 በመቶ በላይ የአባይን ውሃ ባለቤት ነች። ይህ ተፈጥሮ የቸራትና የማንንም መብት ሳትጋፋ ከተፈጥሮ ያገኘችው መብት ነው። ይህ መብት ለዘመናት ዕውቅና ሳይሰጠው ኖሯል። እንደውም ሌሎች አገራት ይህንን ተፈጥሯዊ መብት ወስደው ዜጎቻቸውን በተሳሳተ መንገድ ሲመሩ ቆይተዋል። ፕሮፌሰር አደም እንደሚሉት የአባይን ውሃ አላግባብ መጠቀም የሚፈልጉ አገራት በሰራዊቱም ሆነ በሌላው ዜጋ ሁሉ ሲያሰርፁ የኖሩት 6ሺህ 696 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው (2ሺህ 700 ሜትር ኪዩብ በሰከንድ የሚጓዘውን)ና ከዓለም በትልቅነቱ በቀዳሚነት የሚገኘው ዓባይ ለአንድ አገር ብቻ የተሰጠ፤ ለእነሱ ብቻ የተፈጠረ አድርገው ነው፤ የነበረው ስምምነት የቅኝ ግዛት ስምምነት መሆኑን ዜጎች አያውቁም።

ኢትዮጵያ ዓባይን መገደብ መብቷ ነው። ግዴታዋም ነው። ግዴታዋ የሚሆነው የህዝብ ቁጥሯ እየጨመረ ነው፤ ይህንን ህዝብ መመገብ ያስፈልጋል። ይህ ህዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልገዋል። ይህ አገርና ህዝቡ ከድህነት መውጣት አለበት፤ የስራ እድል መፈጠር አለበት። እንደ አገርና ህዝብ ብዙ ብዙ ነገር መሟላት አለበት። በመሆኑም ዓባይን ገድቦ መጠቀም የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነው። የመኖር ወይም አለመኖር ጉዳይ ነው፤ ከተረጂነት የመውጣት ወይም ያለ መውጣት ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ ነው መታየት ያለበት።

በአለማችን ከ200 በላይ ግድቦች አሉ። አሜሪካ ማንን አማክራ ነው ግድብ የገነባችው? ቻይናን ማን አትገደቢ ብሏት ነበር? ጩኸቱ ምነው እኛ ላይ በዛ? ይህንን ነው እኛ መገንዘብ ያለብን። ተገንዝበንም አንድ ሆነን በመቆም መስራት ያለብን።

ኢትዮጵያ ግድቡን ስትጀምር ሁሉን ነገር ግልፅ አድርጋ ነው። ምንም ነገር ምስጢር ያደረገችው ነገር የለም። አስረድታ ነው፤ አስገንዝባ ነው። ምንም አይነት ጉዳት በግብፅም ሆነ ሌሎች ላይ እንደማይፈጥር አብራርታለች። በጋራ እንስራ ብላለች። ብዙ ርቀት ሄዳለች። አገራት ይህንን ቢያወቁም ኢትዮጵያን ለመተባበር ግን አይፈልጉም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ግልፅ ሲሆን፣ እሱም ከድህነትና ተረጅነት አዙሪት ውስጥ እንዳንወጣ በመፈለጉ ምክንያት ነው።

ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም 10ኛ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው ይህ ታላቁ ግድባችን ገና ከጅምሩ፣ የመሰረት ድንጋይ መጣሉን (መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም) ተከትሎ በሁለት ፈረቃ የሚሰሩ 8ሺህ 500 ሰራተኞችን በማሳተፍ ወደ ስራ የተገባበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን፣ ይህ ወደ ፊትም ምን ያህል የስራ እድል ለዜጎች እንደሚፈጥር ከወዲሁ የሚያመለክት ነው።

ኢትዮጵያ እያደገ ያለውን የህዝብ ቁጥሯን ለመመገብ እና የተሻለ ህይወት እንዲመራ ለማስቻል አባይንም ሆነ ሌሎችን ወንዞች ገድባ ለልማት ማዋል አለባት። ይህ ደግሞ መብቷ ነው።

ኢትዮጵያም ይህንን የልማት ጥያቄዋን በተለያዩ መንገዶች ለአረቡ አለም ማስተማር አለባት። ምንም እንኳን በአሁኑ ሰአት ግድቡን የማደናቀፍ አቅማቸው የተሟጠጠ ቢሆንም ህዝቡ እውነቱን ይገነዘብ ዘንድ ማገዝ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ የተጠቀመችው፤ ወደፊትም የምትጠቀመው የራሷን ሀብት እንጂ የሌላ የማንም አለመሆኑን ማስተማር ያስፈልጋል። ነገም ሌላ ግድብ ይኖረናልና ለዛም ከወዲሁ ማሰብ ተገቢ ይሆናል።

በጥናቶች እንደ ተረጋገጠው ከግድቡ የሚገኘውን ኃይል ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከማዋል ባለፈ የሚተርፈውን ማለትም 2ሺህ ሜጋዋት ያህሉን ለጎረቤት አገራት በመሸጥ በዓመት እስከ 580 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ይቻላል። የዋናው ግድብ ውፍረት የግድቡ ግርጌ ላይ 130 ሜትር ሲሆን፤ የግድቡ ጫፍ ወይም የላይኛው ክፍል ደግሞ 11 ሜትር ነው። የግድቡ የኃይል ማመንጫ ዩኒቶች 13 ሲሆኑ፤ እያንዳንዱ ዩኒት የሚያመነጨው የኃይል መጠን ከ375 እስከ 400 ሜጋዋት ነው። ይህ ለእኛ፣ ለኢትዮጵያዊያን የብልፅግና ተስፋ ነው።

በአሁኑ ሰዓት ሦስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት በመጠናቀቁ አገራት የኤሌትሪክ ኃይል ግዢ ለመፈፀም ጥያቄዎችን እያቀረቡ ይገኛሉ። ለአብነት ኬንያን ብንወስድ።

የኢትዮ- ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ መስመር እና የኮንቨርተር ማከፋፈያ ጣቢያ በይፋ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ጀምሯል። የኃይል ማስተላለፍ የጀመረው የኢትዮ – ኬኒያ ባለ 500 ኪል ቮልት የማስተላለፊያ መስመር በዓመት እስከ 100 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ገቢ የማስገባት አቅም ያለው ነው።

እንዲሁም ከኬንያ አልፎ ከታንዛኒያ እስከ ደቡብ አፍሪካ ላሉት አገራት እስከ 2ሺህ ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ አቅም ያለው መሆኑ ተገልጿል። ኢትዮጵያ ቀደም ብላ ከሱዳን እና ከጅቡቲ ጋር የኃይል ሽያጭ የጀመረች ሲሆን፥ ከሶማሌ ላንድ፣ ታንዛኒያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ለማከናወን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማለች።

በዚህም ባለፈው ዓመት ለሱዳን እና ለጅቡቲ ከቀረበ የኤሌክትሪክ ኃይል 95 ነጥብ 4 ሚሊየን የአሜሪካ ዶሊር ገቢ መገኘቱን መንግስት አስታውቋል። ይህ ለኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ ነው።

የኢትዮጵያ ዕድገት የሚያሳስባቸው አካላት በአገር ውስጥ የተለያዩ ግጭቶችንና ሁከቶችን በመፍጠር አገሪቱ ከተያያዘችው የልማት አቅጣጫ ለማደናቀፍ ሲጥሩ ቆይተዋል። ባለፉት ሁለት አመታት የተካሄደውም ጦርነት የዚሁ አንዱ መገለጫ ነው።

የኢትዮጵያ አካሄድ ያሰጋቸውና ነገ ከነገ ወዲያ ከራሷ አልፋ ሌሎችንም ታነሳሳለች የሚል ስጋት የገባቸው አገራትና ተቋማት ኢትዮጵያ በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትቆይ በርካታ ስራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል። ዓለም አቀፍ ሚዲያዎችም በየዕለቱ የኢትዮጵያ ስም በማንሳት የአገሪቱ ገጽታ እንዲበላሽ በብዙ ሲደክሙ ሰንብተዋል። በዲፕሎማሲው ዘርፍም ኢትዮጵያ ከዓለም ማህበረሰብ የተገለለች እንድትሆን ያለመታከት ሰርተዋል።

አንዳንዶቹም ኢትዮጵያ እንደአገር እንዳትቀጥል የቻሉትን ሁሉ አድርገዋል። ፈርሳለች፤ ሀገር ሆና አትቀጥልም እስከ ማለት ደርሰዋል። ሆኖም ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ተጋድሎ የአገሪቱን ህልውና ማስቀጠል ችለዋል። ፈረሰች የተባለችው አገር ስንዴ አምርታ ወደ ውጭ ኤክስፖርት ማድረግ ችላለች። የአባይን ግድብ ግንባታና ኃይል አመንጭታ ለጎረቤት



**የኢትዮጵያ አካሄድ ያሰጋቸውና ነገ ከነገ ወዲያ ከራሷ አልፋ ሌሎችንም ታነሳሳለች የሚል ስጋት የገባቸው አገራትና ተቋማት ኢትዮጵያ በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትቆይ በርካታ ስራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎችም በየዕለቱ የኢትዮጵያ ስም በማንሳት የአገሪቱ ገጽታ እንዲበላሽ በብዙ ሲደክሙ ሰንብተዋል። በዲፕሎማሲው ዘርፍም ኢትዮጵያ ከዓለም ማህበረሰብ የተገለለች እንድትሆን ያለመታከት ሰርተዋል**

አገራት ብርሀን መሆን ችለላች።

በተለይም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስትና ሕወሓት ሲያደርጉት የነበረውን ጦርነት አቁመው ወደ ሰላም መምጣታቸው ያልተዋጠላቸው አገራትና ግለሰቦች ይህንን የሰላም ሂደት ለማጠልሸት የማይቆፍሩት ድንጋይ የለም። የላም ሂደቱ ተደናቅፎ ጦርነቱ መልሶ እንዲያገረሽና ኢትዮጵያ በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትቆይ የቻሉትን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

የሰብአዊ እርዳታ አልገባም፤ የኤሌትሪክ፤ ቴሌና የባንክ አገልግሎት አልተጀመረም፤ ወዘተ የሚሉ አፍራሽ ትርክቶችን በመፍጠር የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማሳሳት ዘመቻ የጀመሩ አካላትን እየተመለከትን ነው። አንዳንዶቹም አፍ አውጥተው ለሰላም ያላቸውን ጥላቻ ሲናገሩ ተደምጠዋል። የኢትዮጵያ ሰላም የሚመጣው በጦርነት እንደሆነ ያለህፍረት የሚናገሩ የዘመኑ ጉደኞችን ሰምተናል። ሆኖም ኢትዮጵያውያን የሰላምን አስፈላጊነት በአግባቡ የሚረዱ ህዝቦች በመሆናቸው ላለፉት ሁለት አመታት ያነሱትን ነፍጥ ዘቅዝቀው ፊታቸውን ወደ ሰላም መልሰዋል።

ከወዲሁም የተስፋ ወጋገን መውጣት ጀምሯል። መከላከያ ትግራይ ውስጥ ገብቶ ወላድ እናቶችን ወደ ጤና ተቋማት መውሰድ ጀምሯል። የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ፤ ለተቸገሩ ወገኖች ያለውን ምግብ ሲያካፍል አይተናል። ይህ የኢትዮጵያውያንን ሰላምና ዕድገት ለሚመኙ ወገኖች ያስደስታል። በተቃራኒው የኢትዮጵያን ውድቀት ለሚሹ አካላት ንዴትን የሚፈጥር ነው። ስለዚህም ይህንን ሰላም ማጨናገፍና ጦርነቱን ማስቀጠል እነዚህ አካላት ለነገ የሚተውት ተግባር አይደለም።

ባጠቃላይ፣ ኢትዮያ ጠላቶቿ ብዙ ናቸው። በመሆኑም ይህ ግንዛቤ ተይዞ ነው መሰራት ያለበት። ኢትዮጵያ ከወዲሁ ካልተያዘች አትቻልም፤ ሌሎች ስራዎችንም ልቀጥል ትላለች የሚሉት ነገር ሊታሰብበት ይገባል። ኤምባሲዎቻችን አረቢኛ በሚችሉ ሰዎች መሞላት አለበት። ህዝቡ የአገር ጉዳይን አጀንዳው ማድረግ አለበት። በሁለቱም ሀይማኖቶች ተሰሚነት ስላለን እሱን ተጠቅመን መስራት ያስፈልጋል።

አንድነታችንን ካልጠበቅን፤ እየተደገሰልን ያለውን ከወዲሁ ተረድተን ለመፍትሄው ካልሰራን በኋላ ብዙ ዋጋ ሊያስከፍለን እንደሚችል ማወቅ አስፈላጊ ነው። በመከላከያ በኩል አስፈላጊው ዝግጅትና ጥንካሬ ሊኖር የግድ ነው።

በዲፕሎማሲው መስክም የተጀመሩ ጥረቶች ወደ ኋላ መመለስ የለባቸውም። ባለፉት ሁለት ዓመታት በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ ስም በብዙ ጎድፏል። ስለዚህም በዲፕሎማሲው ዘርፍም ሆነ በሚዲያው በኩል ይህንን ገጽታ ወደ ነበረበት መመለስ ይጠይቃል።

ሚዲያዎቻቸው በየቀኑ በተለያዩ ቋንቋዎች በእኛ ላይ የሚያካሂዱትን ዘመቻ በመቀልበስ መታገል ይገባል። የሰላም ስምምነቱ ስለተፈረመ ብቻ የውጭው አለም በአንድ ጊዜ ከኢትዮጵያ ጎን ይቆማል ማለት ዘበት ነው። ስለዚህም ስለ ኢትዮጵያ በየቀኑ ማሰብ፤ መስራትና ውጤት ማምጣት የሁላችንም ግዴታ ሊሆን ይገባል በማለት ረ/ፕ አደም ካሚል ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ተፈጥሮ ተኮር የስራ ፈጠራዎች በወጣቶች

እስናቀ ፀጋዬ

ከዓመታት በፊት የአዲስ አበባ ከተማ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ክምሩ ሲደረመስ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች መሞታቸውን በዜና ሰማች። ለዚህም ከብዙ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ፌስታል በብዛት በቆሻሻ ውስጥ መኖሩ እንደሆነ ተረዳች። እነዚህ ፌስታሎች በቆሻሻ ውስጥ ሲኖሩ ተፈጥሯዊ የሆነው ቆሻሻ ከመሬት ጋር እንዳይገናኝ እንቅፋት እንደሚሆንበትም አወቀች።

በተለይ ፌስታል በባህሪው ትንሽ ነገር ሲጫነው ቆሻሻ እንደሚያንሸራትትና በውስጡ ውሃ ሲቋጥር ደግሞ "ሜቴይን" የተሰኘ ጋዝ እንደሚፈጠርና ይህም ኦክስጂን ካገኘ እንደሚፈነዳ ተገነዘበች። ምን አልባትም የአዲስ አበባ ቆሻሻ ለመደርመሱ ይህ ሌላኛው ምክንያት ሳይሆን እንዳልቀረም አረጋገጠች።

ይህን ክስተት ተከትሎ ከአካባቢ ጋር የሚስማማና ፌስታልን ሊተካ የሚችል የጨርቅና የወረቀት ቦርሳ ማምረት እንዳለባት ከራሷ ጋር መከረች። ሆኖም ይህ ስራ መነሻ ካፒታሉ ከፍ ያለ በመሆኑና ከፌስታል ዋጋ ጋር በገበያ ተፎካካሪ መሆን ባለመቻሉ ስራውን አቆመች።

ከእጅ የሚሰሩ የጨርቅ ቦርሳዎችን ለምን አልሰራም በሚልና እዛው ቆሻሻው የተደረመሰበት አካባቢ ለሚኖሩ ሴቶች የስራ እድል አልፈጥርም ብላ በማሰብ ጨርቅን ከቆዳ ጋር በማዋሃድ ቦርሳዎችንና ዋሌቶችን የሚያመርት ድርጅት አቋቋመች፤ የቱባ ጨርቅና ቆዳ ውጤቶች አምራች ድርጅት መስራችና ባለቤት ወጣት ቅድስት ተስፋዬ።

ተፈጥሮ የለገሷትን መልሳ በእጥፍ ለመቸር ወደኋላ አትልም። የተንከባከቧትን ያህል ደርባ ትሰጣለች። የዛኑ ያህል ደግሞ እርሷን የሚፈታተኑና የሚጎዱ ተግባራትን መፈፀም ምላሹ የከፋ እየሆነ መጥቷል። ለዚህም በደን መጨፍጨፍ ምክንያት እየተስፋፋ የመጣው በርሃማነትና ወደአየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች አማካኝነት የተከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ አንዱ ማሳያ ነው።

በሰው ልጆች አማካኝነት ተፈጥሮን የሚጎዱ ተግባራት አሁንም እየተፈፀሙ በመሆናቸው ተፈጥሮ በሰው ልጆች ላይ የምታሳርፈው የቅጣት በትር ከእለት እለት እየጨመረ መጥቷል። ነገር ግን አሁን አሁን የሰው ልጅ በጥቂቱም ቢሆን ከጥፋቱ እየተማረ የመጣ ይመስላል። ፊቱንም ወደ ተፈጥሮ እያዞረ ነው።

በርካታ ስራ ፈጠራዎችም ተፈጥሮን መሰረት እያደረጉ መጥተዋል። በኢትዮጵያ በጥቂቱም ቢሆን በወጣቶች የተጀመሩ አንዳንድ ተፈጥሮ ተኮር የስራ ፈጠራዎች ብቅ ብቅ እያሉ ነው። የወጣት ቅድስት ተስፋዬ የስራ ፈጠራም ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

ወጣት ቅድስት ድርጅቱ ማህበረሰብ ተኮር አካባቢን፣ ማህበረሰቡንና የኢኮኖሚውን ሚዛን ጠብቆ የሚንቀሳቀስ መሆኑን ታስረዳለች። የስራ እድል መፍጠር የድርጅቱ አንደኛው አላማ ሆኖ በቅድሚያ ከስራው ጋር በተገናኘ ለሴቶችና ለወጣቶች ስልጠና ሰጥቶ ጥሬ እቃ በማቅረብ ከቤታቸው ሆነው ስራውን እንደሚያከናውኑ ትገልፃለች። ይህም ስራ ማህበረሰብ ተኮር መሆኑን እንደሚያሳይ ትጠቁማለች።

ከአካባቢ ጋር በተያያዘም ድርጅቱ የሚጠቀምባቸው ጥሬ እቃዎች 30 ከመቶ መልሶ ጥቅም ላይ ከሚውል ጨርቅና 70 ከመቶ ጥጥ ተቀላቅሎ ከሚሰራ ክር መሆኑንም ወጣት ቅድስት ተናግራ፤ ይህን ክር በመጠቀም ጨርቁን እንደሚሰሩም ነው የምታብራራው። ይህንኑ ጨርቅ እንደ ጥሬ እቃ በመጠቀምና ከቆዳ ጋር በማዋሃድ ሴቶች ከቤታቸው ሆነው ቦርሳዎችን በተለያዩ ዲዛይኖች እንደሚያመርቱ ታስረዳለች።

እያንዳንዱ ሰው ወደከባቢ አየር የሚለቀው የካርበን መጠን አለው የምትለው ወጣት ቅድስት፤ ከዚህ አንፃር ሴቶቹ ከቤታቸው ሆነው መስራታቸው በእንቅስቃሴያቸው ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የካርበን ልቀት በመቀነስ ረገድ አስተዋፅኦው የጎላ መሆኑን ትጠቅሳለች። እነዚህ ሴቶች ትራንስፖርት ተጠቅመው ሌላ ቦታ ሄደው ቢሰሩ ወይም ጨርቁን ለማምረት ማሽን ቢጠቀሙ ኖሮ



ወጣት ቅድስት ተስፋዬ፤


ወጣት ሄኖክ ስዩም፤

ሊያወጡት የሚችሉት የካርበን መጠን እንደሚኖርና ከቤታቸው ሆነው በእጃቸው በመስራታቸው ግን የካርበን ልቀት መጠኑን እንደሚቀንስ ታብራራለች።

የድርጅቱ ደምበኞች ከውጪ አገራት በተለይ ከቻይና የሚመጡ ቦርሳዎችን ቢጠቀሙ ቦርሳዎቹ ሲመረቱ። ተጓጉዘው ተጠቃሚው ጋር እስኪደርሱ የካርበን ልቀት ስለሚከሰትባቸው ሰዎች ሲገዟቸውም ይኸው የካርበን መጠን በቦርሳው ላይ ስለሚያርፍ በገዢዎች ላይ የራሱን የሆነ የጤና ጉዳት እንደሚያደርስም ታብራራለች።

ከዚህ አንፃር ድርጅቱ ዓልሞ የተነሳው ሰዎች የካርበን መጠን ያለባቸውን ቦርሳዎች ትተው ዳግም ጥቅም ላይ በሚውሉ ጥሬ እቃዎች በእጅ የተዘጋጁ ቦርሳዎችንና ዋሌቶችን እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው። ሰዎች በቻይና አልያም በሌላ አገራት የሚመረቱ ቦርሳዎችን ገዝተው ከሚጠቀሙ የድርጅቱን ምርት ቢገዙ ወደነርሱ የሚለቀቀው ካርበን ሊጠፋላቸው እንደሚችልም ትጠቁማለች።

እንደ ዓለም የካርበን ልቀት መጠንን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ድርጅቱ እያከናወነ ያለው ስራ ከፍ ያለ አስተዋጾ የሚያበረክት መሆኑን ነው ወጣት ቅድስት የምትናገረው።

ድርጅቱ ሴቶቹ በየቤታቸው ያመረቱትን ተቀብሎ በአዲስ አበባ ባለው መሸጫ መደብር ለተጠቃሚዎች እንደሚያቀርብም ነው የምትገልፀው። ሴቶቹ ባመረቱት ልክ ክፍያ እንደሚያገኙም ነው የምትጠቅሰው። እነዚህ ምርቶች ጥቅም ከሰጡ በኋላ በቀላሉ በመሬት ውስጥ የሚበሰብሱና ከአካባቢ ጋርም ተስማሚ መሆናቸውን ወጣት ቅድስት ታስረዳለች።

ድርጅቱ ከ30 በላይ የሚሆኑ ሴቶችንና 3 ወንዶች አምራቾችን ይዞ ምርቱን እያመረተ መሆኑንና የማምረት አቅሙም ከግዜ ወደ ግዜ እያደገ መምጣቱን ጠቁማ በቀን እስከ 50 ቦርሳዎችን የማምረት አቅም እንዳለውም ትጠቅሳለች። ከዚህም በላይ ማምረትና ከስራ እድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ ተደራሽነቱን ማሳደግ እንደሚፈልግም ታክላለች።

ይሁንና የመስሪያ ቦታ እጥረት እንዳለ ወጣት ቅድስት ገልጻ ከዚህ አንፃር የሚመለከተው አካል ችግሩን መፍታት ቢችል ድርጅቱ ከዚህም በላይ የማምረት አቅም እንዲሁም ለተጨማሪ ወጣቶች የስራ እድል የመፍጠር ፍላጎት እንዳለው ትናገራለች።

በተጨማሪም ድርጅቱ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ መልሶ ጥቅም ላይ መዋል በሚችሉ ነገሮች ዙሪያ ለሴቶች ስልጠና የመስጠት ውጥን እንዳለውም ትገልፃለች።

**በሰው ልጆች አማካኝነት ተፈጥሮን የሚጎዱ ተግባራት አሁንም እየተፈፀሙ በመሆናቸው ተፈጥሮ በሰው ልጆች ላይ የምታሳርፈው የቅጣት በትር ከእለት እለት እየጨመረ መጥቷል። ነገር ግን አሁን አሁን የሰው ልጅ በጥቂቱም ቢሆን ከጥፋቱ እየተማረ የመጣ ይመስላል። ፊቱንም ወደ ተፈጥሮ እያዞረ ነው**

በአገሪቱ ላለው ችግር እንደ አንድ ምክንያት የሚታየው ስራ አጥነት መሆኑን ድርጅቱ እንደሚያምንበት ገልጻ በቀጣይም ድርጅቱ የስራ እድል ፈጠራን እንደ ዋነኛ ተልእኮው በመያዝ እንደሚንቀሳቀስ ትጠቁማለች።

ወጣት ሄኖክ ስዩም ኢኖቬክስ ሀንድክራፍትስ የተሰኘው ከወዳደቁና ጥቅም ከማይሰጡ እቃዎች የእደ ጥበብ ውጤቶችን የሚያመርት ድርጅት መስራችና ባለቤት ሲሆን በመጀመሪያ እርሱና ባለቤቱ ቀለል ያለ ቢዝነስ ለመጀመር እንዳሰቡ ያስታውሳል። በመቀጠልም አካባቢን የማይበክሉ፣ ይልቁንም የሚጠብቁና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን ሊተኩ የሚችሉ የእደ ጥበብ ውጤቶችን ወደማምረት መግባታቸውን ይናገራል።

በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ የሚሰራቸው የእደ ጥበብ ውጤቶች ቤት ውስጥ ከወዳደቁና ጥቅም የማይሰጡ እቃዎች የሚሰሩ መሆኑን ወጣት ሄኖክ ይናገራል። እነዚህም ቤትን የሚያስውቡ የአበባ ማስቀመጫ፣ የፊት መስታወት፣ የእስክሪቢቶ ማስቀመጫና ሌሎችም መሆናቸውን ይጠቅሳል። እነዚህም ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ፣ ጥቅም ከሰጡም በኋላ በቀላሉ የሚበሰብሱና መኖሪያ ቤትን የሚያስውቡ መሆናቸውን ያስረዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ምርቶች ከውጪ የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች በመተካት የውጪ ምንዛሬ እንደሚያድኑም ነው ወጣት ሄኖክ የሚጠቁመው። ምርቶቹ ከወዳደቁና አካባቢን ከማይበክሉ እቃዎች የሚዘጋጁ በመሆናቸው ተጨማሪ የስራ እድል የሚፈጥሩ ስለመሆናቸውም ያብራራል። በአዲስ አበባ ብቻ ከየቤቱ 0 ነጥብ 4 ኪሎ ግራም የማይፈለጉ እቃዎች በየቀኑ ከቤት እንደሚወጡና እያንዳንዱ ሰው እነዚህን የማይፈለጉ እቃዎች ጥቅም ላይ ማዋል ቢችል ለራሱም ሆነ ለሌሎች የስራ እድል መፍጠር እንደሚቻል ነው የሚናገረው።

ስራውን ሲጀምሩ በቀላሉ እንደነበር የሚያስታውሰው ወጣት ሄኖክ በሂደት ምርቶቻቸውን ወደገበያ ይዘው ሲወጡ ቀስ በቀስ ተቀባይነት እያገኙ ስለመጡ የምርት ማሳያ ቦታ መከራየቱን ይጠቁማል።

በአሁኑ ወቅት ከወዳደቁ እቃዎች የሚያመርቷቸውን ምርቶች በስፋት አጠናክረው ማምረት። አሁን ካሉት አራት ሰራተኞች ተጨማሪ የሰው ኃይሉን ማጠናከር። በስፋት ወደማምረቻ ኢንዱስትሪው መግባት እቅዳቸው መሆኑን ገልጿል።

ምርቱ በገበያ ውስጥ የገባ ቢሆንም ህብረተሰቡ ወደነዚህ ምርቶች ፊቱን እንዲያዞር ምርቶቹን ይበልጥ በማሳመር ወደገበያ ለመውጣት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም ነው ወጣት ሄኖክ የሚያስረዳው።

# ቅንጅታዊ ሥራ ለማዕድን ዘርፉ እድገት

ስምስም መንግሥቱ

ከህዳር 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለሶስት ቀናት ለህዝብ ክፍት ሆኖ የቆየው በኢትዮጵያ የተካሄደው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ የዘርፉን ተዋናዮች ብቻ ሳይሆን፣ የተለያዩ ጎብኝዎችንም ቀልብ የሳበ እንደነበር በማጠቃለያ ፕሮግራሙ ላይ ተገልጿል።በህብረቀለማቸው የሚያምሩ የተለያዩ የከበሩ ማዕድናትና ጌጣጌጦችን ይዘው በኤክስፖው ላይ የቀረቡትም ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኘው የማዕድን ሀብት ለጎብኝዎች በማስረዳትና በማስተዋወቅ ጭምር ሚናቸውን ሲወጡም ተስተውሏል።እንዲህ በኤክስፖው ሚናቸውን ሲወጡ ከነበሩት መካከል ደግሞ ሶዞ የተባለው የማዕድን ጌጣጌጥ ላኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ይጠቀሳል።

የኩባንያው ባለቤት ወይዘሮ ባንቻለም ማሩ በኤክስፖው ስለነበራቸው የሶስት ቀናት ቆይታቸው እንደገለጹልን ፤ኩባንያቸው እሴት የተጨመረባቸውን የማዕድን ውጤቶች ለገበያ ለማቅረብ ብቻ ሳይሆን፣ የ15 አመት የሥራ ተሞክሮውንም ለሌሎች ልምድ ይሆናል፣ እግረመንገድም የኢትዮጵያን የማዕድን ሀብት ከውጭ ለሚመጣው ለማስተዋወቅ በሚል እሳቤ ነው ኤክስፖው ላይ የተሳተፈው።ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የተለያዩ የከበሩ ማዕድናት ሀብት ባለቤት ስለመሆኗ የማያውቁ ዜጎች መኖራቸውን ለመገንዘብ ችለዋል።ለብዙዎች በማስረዳትና ለጥያቄዎቻቸውም ምላሽ በመስጠት ጭምር ሚናቸውን ሲወጡ ነበር።ኤክስፖው እንዲህ ያለውን እድል በመፍጠሩ ብዙዎችንም በዘርፉ ለመሰማራት የሚያነሳሳ ግንዛቤ ያስጨበጠ ሆኖ አግኝተውታል።

ኢትዮጵያ ሰፊ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል ሊሰማራበት የሚችል የማዕድን ሀብት ባለቤት እንደሆነች በዘርፉ በሥራ በቆዩባቸው አመታት ለመረዳት መቻላቸውን የሚናገሩት ወይዘሮ ባንቻለም ትውልዱ ስለሀገሩ ሀብት አውቆና ተገንዝቦ በሥራውም የሚሰማራበት ምቹ ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት ያምናሉ።በዘርፉ የሚሰማራ ኢትዮጵያዊ በቁጥር ሲበዛ በዓለም ገበያ ላይ ተጽዕኖ መፍጠር እንደሚቻልም ገልጸዋል።እርሳቸው እንዳሉት እስካሁን ባለው ተሞክሮ በዓለም ገበያ ላይ ዋጋውን እየወሰኑ ያሉት የማዕድኑ ባለቤቶች ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ፣ ገዥዎቹ ናቸው።ይህ አካሄድ ደግሞ ማዕድን አልሚውን፣ እሴት ጨምሮ ለገበያ የሚያቀርበውንም ሆነ ሀገርንም በገቢ ተጠቃሚ እያደረገ አይደለም።ልማቱን በጋራ በማጠናከርና በቴክኖሎጂ አግዞ ማከናወን ሲቻል የገዥዎችን ተጽእኖ ማስቀረትና የሀገርንም ጥቅም ማስጠበቅ ይቻላል።እንዲህ ያለው ኤክስፖም አቅም በመፍጠር ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል።

ወይዘሮ ባንቻለም፣ ባባታቸው እግር ተተክተው ሥራው ውስጥ ቢገቡም የማዕድን ዘርፍ መልካም ዕድሎችም፣ ተግዳሮቶችንም እንዳሉት በ15 አመት ተሞክሮአቸው አይተዋል።እርሳቸው እንዳሉት ስለማዕድን አይነቶች ማወቅና ዘርፉን በእውቀት መምራት አንዱ ክፍተት ወይንም ተግዳሮት ሲሆን፣ ገበያ መፈለግ ደግሞ ሌላው ችግር ነው።ተምሮ እራስን ለማብቃት በሀገር ውስጥ በዘርፉ የሚሰጥ ትምህርት አለመኖርም ፈተና ነበር የሆነባቸው።ከቤተሰብ የወረሱትና በፍላጎትም የገቡበት ዘርፍ በመሆኑ በድረገጽ (ኦንላይን) ትምህርት በመከታተል እራሳቸውን በማብቃት እስካሁን በዘርፉ ለመቆየት ችለዋል።እርሳቸውም ለልጃቸው እውቀት በማካፈልና ስለሥራው ግንዛቤ እንዲኖረው ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።መልካም እድል ብለው ከጠቀሷቸው መካከል ደግሞ የራስን ሀብት (ካፒታል) ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን ነው።በተለያዩ የዓለም ሀገራት በሚካሄዱ የማዕድን ኤክስፖዎች ላይ በመሳተፍ በተገኘ ልምድ ሀብቱን ለገበያ ከማቅረብ ወደጌጣጌጥ በመቀየር የዓለም ገበያ ፍላጎትን ለማሟላት የሚደረገው ጥረትም ሌላው የአቅም ማሳደጊያ መንገድ እንደሆነ ይጠቅሳሉ።ወይዘሮ ባንቻለም «ከተኛንበት እንንቃ» በማለት በዘርፉ ላይ የሚገኘውም አዲስ ለመሰማራት ፍላጎት ያለውም በጋራ ተባብሮ ዘርፉን በማሳደግ እራሱንም ሀገርንም ተጠቃሚ እንዲያደረግ መልእክት አስተላልፈዋል።ኢትዮጵያ ወደ ሀብትነት የሚቀየርና ኢኮኖሚዋንም ከፍ ሊያደረግ የሚችል የምድር ውስጥ ፀጋ እያላት መጠቀም ባለመቻሏ በእድገት ወደኋላ መቅረቷ እንዲህ ቁጭት እየፈጠረ መሆኑን ነው ከወይዘሮ ባንቻለም መልእክት መገንዘብ የሚቻለው።



**የማዕድን ዘርፉ አሁን ላይ ለክፍለኢኮኖሚው እያበረከተ ካለው የአንድ በመቶ ድርሻ በሚቀጥሉት 14 እና 15 አመታት ከ17 በመቶ በላይ ድርሻ እንደሚያበረክት ይጠበቃል፡፡ለስኬታማነቱም የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎችን ከመውሰድ ጀምሮ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በመከናወንም ላይ ይገኛል**

ኢትዮጵያ በሀብት ላይ ሆና የሀብቱ ተጠቃሚ መሆን አለመቻሏ ብቻ ሳይሆን፣ አሁን ላይ የማዕድን ውጤቶች በሆኑ በአንዳንድ ዘርፎች ላይ እየገጠማት ያለው የአቅርቦትና የዋጋ መናር ፈተና የበለጠ ቁጭትን እየፈጠረ እንደሆነ ኤክስፖውን ያዘጋጀው ማእድን ሚኒስቴር ባካሄደው የኤክስፖ ማጠቃለያ መርሃግብር ላይ በአንዳንድ ተሳታፊዎች ተነስቷል።መርሃግብሩ የተካሄደው የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሺዴ፣ የፕላንና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ፍጹም አሰፋ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ፣ በተገኙበት ሲሆን የተለያዩ ጥያቄዎችም ቀርበው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

በመርሃግብሩ ተሳታፊ ከነበሩት የግልና የምንግሥት ተቋማት አንዱ ሜድሮክ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጀማል አህመድ በዚሁ ወቅት፤ መንግሥት ማዕድንን የብልጽግና ምንጭ ነው ብሎ አቋም መውሰዱ አግባብ እንደሆነና በተግባር የሚታይ ለውጥ ዘርፉ ላይ እያሳየ መሆኑን አመልክተዋል።በተለይም ዘርፉን እየመራ የሚገኘው ማዕድን ሚኒስቴር ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ከተጠናከረና ክልሎችም ከታገዙ በሀገር ደረጃ በዘርፉ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚመጣ ተስፋ አድርገዋል።ግብርናውም ሆነ የኢንደስትሪ ዘርፉ ግብአቶችን የሚወስደው ወይንም የሚያገኘው ከማዕድን እንደሆነም አመልክተዋል።የግንባታው ዘርፍ ደግሞ ዋና መሠረቱ ማዕድን እንደሆነ መዘንጋት እንደሌለበትም ገልጸዋል።ግብአቱን ሀገር ውስጥ በሚገኝ ሀብት መጠቀም እየተቻለ ሙሉ ለሙሉ ከውጭ በሚከናወን ግዥ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን አስታውሰዋል።በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለይቶ መፍትሄ በመስጠት በተጠቃሚነት ላይ መሰራት እንዳለበት ሀሳብ ሰጥተዋል።

አቶ ጀማል እንዳስረዱት በአሁኑ ጊዜ ለግንባታው ዘርፍ የሚውሉ ግብአቶች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም የማዕድን ውጤቶች በሆኑ በሚሰሩት ላይም ተግዳሮት እያጋጠመ ነው።ለአብነትም እንዳነሱት እያንዳንዳቸው አምራች ፋብሪካዎች ለማሞቂያ የሚውል ኃይል የሚጠቀሙበት ግብአት በውጭ ምንዛሪ ተገዝቶ ሀገር ውስጥ በሚገባ ፈርነስአይል በተባለ የማዕድን ግብአት ነው።ይሄንን ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ መተካት የሚያስችል እምቅ ሀብት ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛል።ሀብቱ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ከፀጥታ፣ ከመሬት አቅርቦት በአጠቃላይ ከመሠረተልማት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመፍታት ለአምራች ኢንደስትሪዎቹ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ እሴት በመጨመር ተዘጋጅቶ በፍጥነት ለማቅረብ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

አቶ ጀማል ከወርቅ ማዕድን ጋር በተያያዘም እንደገለጹት፣ እስካሁን ባለው ተሞክሮ በወርቅ ማዕድን እርሳቸው ከሚመሩት ኩባንያ ውጭ ያሉት ምርታማነታቸው ከአቅምበታች ነው።እነዚህን አነስተኛ ወርቅ አምራቾች አቅም በማሳደግ ምርቱ ከፍ እንዲል ማድረግ ከመንግሥት ይጠበቃል።ወደ ማምረት ለመሸጋገር በሂደት ላይ የሚገኙትም ቢሆኑ በፖሊሲና በተለያየ መንገድ የመንግሥት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።የሀገር ኢንቨስትመንትን በመሳብ ከውጭ የሚመጣው ባለሀብት ተግዳሮቶችን ተሸክሞ የሚጓዝ እንዳልሆነም መረዳት ያስፈልጋል።ኢትዮጵያዊው ባለሀብት ሌላ ሀገር ስለሌለው ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ለመሥራት ዝግጁ ነው።ይህን ዝግጁ የሆነ ባለሀብት ደግሞ ከውስጥ አስተዳደር ጀምሮ በተለያየ መንገድ በአቅም ግንባታ በማጠናከር ደግፎ ውጤታማ ማድረግ ይጠበቃል።በዚህ ረገድ ያለውን የቤት ሥራ ለመወጣት በመንግሥት በኩል ስላለው የቤት ሥራ በእለቱ ለተገኙት ለገንዘብ ሚኒስትሩና ለሌሎቹም ጥያቄ አቅርበዋል።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርን ወክለው የተገኙት ተሳታፊም በሰጡት ሀሳብ፤ ሲሚንቶና ለግንባታ ማጠናቀቂያ የሚውሉ ሴራሚክ የመሳሰሉ ግብአቶችን በመጠቀም የግንባታው ዘርፍ ከፍተኛ ድርሻ ይወስዳል።ኢኮኖሚው እያደገ ሲሄድ፣ የሲሚንቶ ፍጆታውም አብሮ ያድጋል።አሁን ሀገር በምትገኝበት የኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ የሲሚንቶ አቀርቦትና ግንባታው የሚፈልገው ግብአት የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም።በዚህ የተነሳም ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ የግንባታ እንቅስቃሴ ፈተና ውስጥ ወድቋል።እንደ ተወካዩ ሀሳብ ይህ ችግር የተፈጠረው ኢትዮጵያ ውስጥ 98 በመቶ የሚሆን ለሲሚንቶ ግብአት የሚውል ሀብት እያለ ነው።የግብአት እጥረት ሊያጋጥም ቀርቶ በዋጋም ቢሆን ባነሰ ሽያጭ መገኘት መቻል ነበረበት።ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ላይ በፋብሪካ የሲሚንቶ የመሸጫ ዋጋ በሌላው ዓለም ላይ ከሚሸጠው ጋር እንኳን ለውድድር የሚቀርብ አይደለም።እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ነው።በሚቀጥለው አስር አመት በኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ የግንባታው ዘርፍ መፋጠን ወሳኝ ነው።ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋ አድጎ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት መካከል አንዷ ሆና ለመገኘት የግንባታው ዘርፍ ወሳኝ ነው።የግብርናውም ሆነ የቱሪዝም ኢንደስትሪው፣ ሌላውም ከግንባታ ጋር ይያያዛል።እንደ ሴራሚክ ለመሳሰሉ የግንባታ ማጠናቀቂያዎች የሚውል ጥሬ ሀብት ኢትዮጵያ ውስጥ እያለ በግዥ ከውጭ ገብቶ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል።የሲሚንቶ ፍላጎትን ማሟላት የሚችል አቅም እየፈጠረች ስላለችው ጎረቤት ሀገር ኬኒያንም ለአብነት ጠቅሰዋል።ከወዲሁ ካልታሰበበት ወደፊት በእቅድ የተያዙ የግንባታ የልማት እቅዶች እንዳይስተጓጎሉ ሥጋታቸውን ገልጸዋል።በጋራ በመሥራት ክፍተቶችን ለመሙላት እየተደረገ ስላለው ጥረትም ጥያቄ አቅርበዋል።

ሌሎችም ተሳታፊ የኩባንያ ባለቤቶች በዘርፉ ላይ ያሉ ማነቆዎችንና ክፍተቶችን አንስተዋል።አንዳንዶችም መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት በማጠናከር ለተሻለ ውጤት እንዲሰራ ጠይቀዋል።በዘርፉ ላይ የሚኘውም ባለሀብት በተበታተነና በተበጣጠሰ መንገድ ከሚንቀሳቀስ ተደራጅቶ አቅም ፈጥሮ በጋራ እድገት የሚያስመዘግብበትን ሁኔታ ቢፈጥርና በዚህ ረገድም መንግሥት እገዛ ቢያደርግ መልካም እንደሆነ ሀሳብ ቀርቧል።

መንግሥትን ወክለው የተገኙትም ከፍተኛ አመራሮች የየድርሻቸውን የቤት ሥራ መውሰዳቸውን በምላሻቸው አረጋግጠዋል። የገንዘብ ሚኒስትር አህመድ ሺዴ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ኢንቨስት ያደረጉ ባለሀብቶች በተለይም ወቅታዊ በሆኑና በተለያዩ ምክንያቶች ባጋጠሙ ችግሮች ውስጥ ጫናዎችን ተቋቁመው ከፍተኛ ሥራ እየሰሩ የሚገኙ ኩባንያዎች መደገፍ አለባቸው በሚል ከአንዳንድ ተሳታፊዎች የቀረበው ሀሳብ ተገቢነት ያለው መሆኑን ገልጸዋል።በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ውጤታማ ሥራ የሰሩት መደገፍ አለባቸው ተብሎ የተነሳው ሀሳብ በመንግሥትም የታመነበት ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል።ኢንቨስትመንት እንዲበረታታና የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን መንግሥት የሚችለውን ሁሉ የሚያደርግና የሚደግፍ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ እንደተናገሩት ኮሚሽኑ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ያበረታታል። ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያም እንዲያቀርቡ፣ ግብአቶችንም ከውጭ ወደ ሀገር እንዲያስገቡ የሚገጥማቸውንም ተግዳሮት በመፍታት፣ ለውጭ ኢንቨስተሮችም ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ኮሚሽኑ የሚጠበቅበትን ተልእኮ ለመወጣት ዝግጁ ነው።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ፤ ባለሀብቱ ሰብሰብ ብሎ አቅም ቢፈጥር የተሻለ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል በሚል ከተሳታፊዎች የቀረበውን ሀሳብ ተጋርተዋል።ዘላቂ የሆነና ሀገር የምትኮራበት ልማት ሊመዘገብ የሚችለው የሀገር ውስጥ ባለሀብት በሚያደርገው ጥረት እንደሆነም ገልጸዋል። በአስተያየትና በጥያቄ የቀረቡት አንዳንድ ሀሳቦች መንግሥት የሚወስዳቸው የቤት ሥራዎች መሆናቸውንም አመልክተዋል።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ዑማ፤ እንደሀገር በግብርናውና በሌሎችም የክፍለኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የተመዘገቡትን ውጤቶች በማዕድን ዘርፍም የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረቶች ተጠናክረዋል። የማዕድን ዘርፉ አሁን ላይ ለክፍለኢኮኖሚው እያበረከተ ካለው የአንድ በመቶ ድርሻ በሚቀጥሉት 14 እና 15 አመታት ከ17 በመቶ በላይ ድርሻ እንደሚያበረክት ይጠበቃል።ለስኬታማነቱም የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎችን ከመውሰድ ጀምሮ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። በመከናወንም ላይ ይገኛል።

ማዕድን ውድና በክፍለኢኮኖሚ እድገት ላይ ለውጥ የሚያስገኝ ስለመሆኑ እንዲህ በተለያዩ የምንግሥት ሀላፊዎችና በዘርፉ ተዋናዮች ተነስቷል። አላቂ የሆነውን ይህን ውድ ሀብት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የአመራረት ዘዴ በመታገዝ ከብክነት ማዳን፣ ለህገወጥ ተጋላጭነቱን ማስቀረት፣ የግጭት መንስኤም እንዳይሆን መሥራት ይጠበቃል።የማዕድን አምራቾች፣ ላኪዎች፣ አማካሪዎችና ሌሎችንም የዘርፉ ተዋናዮች ካሳተፈው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ዓለምአቀፍ ኤክስፖ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች በመቀመር በሚቀጥለው ጊዜ በተሻለ ለማዘጋጀት ማቀዱን ማዕድን ሚኒስቴር አረጋግጧል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ዓለም በቃኝ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከአምስት ዓመት በኋላ ከሮዛ ጋር ተጋባን።ያን ወፍ ዘራሽ ወንድነቴን ባሏ አደረገችው።ያን በተለያዩ ሴቶች ያደፈ ገላዬን አቅፋው ልትተኛ ነው..ያን በብዙ ሴት የተሳመ ከንፈሬን ልትስመው ነው።

ወፍ ዘራሽ ነበርኩኝ እኮ..አብረን የሚያዩን አንዳንድ ሰዎች ወደ እኔ እየጠቆሙ ‹ይሄን ሰው ብላ አገባችው? ይሏታል።ታሪኬን የሚያውቁ አንዳንድ ጓደኞቿ ከእኔ ጋር በመጣመሯ ‹ምን አስነከቶሽ ነው ግን? ሲሉ ፊታቸውን አቀጭመው ይጠይቋታል።ለሁሉም የሚሆን መልስ አላት።

ምኔን እንደወደደችው አላውቅም።ሰው ምግባሩ ካላማረ የሚወደድ ነገር እንደሌለው ነበር የማውቀው።ከምግባርም፣ ከባህሪም፣ ከመልክም ምን የሌለኝ ሰው እዛች ልዕልት ላይ መውደቄን ሳስብ ያልነቃሁት..ወደፊት የምነቃው ህልም ያለ ይመስለኛል።

ትላንት ሌላ ነበርኩ..ዓለም ውንብድናዬን የሚገልጽ ቃል የላትም።በእየሱስ ግራና ቀኝ ከተሰቀሉት ወንበዴዎች የማልስተካከል፣ ሌንጊኖስ ብትሉ፣ አሪዮስ ብትሉ፣ ኒቼና የሞት ነጋዴው ቤልጎፌር የማይልቁኝ ምንም ነበርኩ።በዚች ሴት ፊት ባለማዕረግ ተባልኩ።

ደስታዬ ሀጢዐት ነበር። እንደ እኔ በሀጢዐት የሚደሰት ሰው አልነበረም።ስለሀጢዐት እያሰብኩ ተኝቼ ስለ ሀጢዐት እያለምኩ ከእንቅልፌ እነቃለው።ብቻዬን ተኝቼ አላውቅም.. በግራና በቀኜ ሁሌም ሴቶች አሉ።ማታ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደተቀራረብኳቸው የማላስታውሳቸው ሴቶች ጠዋት ላይ ክንዴን ተንተርሰው አብረውኝ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ አያለሁ.. ይሄ ነው ጠዋቴ።ሀጢዐት እያሰቡ ከእንቅልፍ መንቃት፣ ሀጢዐት እየሰሩ መዋልና ሀጢዐት እየሰሩ ማደር..ይሄ ነው ወንድነቴ።ሮዛ ይሄን ሰው ባሏ አደረገችው..

አንድ ቀን እንደኔ ሀጢዐት በሚያረካቸው ወንድና ሴቶች ተከብቤ እየጠጣሁ በተቀመጥኩበት የቅዳሜ ማግስት አርብ ላይ ግሮሰሪው ውስጥ ከዚህ በፊት አይቻት የማላውቃትን ጠይም ሴት አየሁ።ለአይኔም ለቤቱም አዲስ እንደሆነች ስላወኩ ዛሬ ከዚች ሴት ጋር ለመጠጣትና ሀጢዐት ልሰራ አስቤ ወዳለችበት ሄድኩ።

‹ሀይ..! አልኳት ወደመስከር በተቃረበ፣ ለመንተፋተፍ ባልደረሰ ሩብ ጉዳይ ድምጽ።

ምን ሀሳብ ላይ እንደሆነች እንጃ ድንግጥ ባላ ድምጼን ወደሰማችበት ዞረች።እንዳልሰማችኝ ሳውቅ እጄን ለሰላምታ ዘረጋሁላት።

ግራ እጇን ቀኝ እጇ ላይ ጣል አድርጋ በጨዋ ደንብ ለታላቅ በሚቀርብ የሰላምታ አይነት እጄን ጨበጠችኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ በጨዋ ሴት ተጨበጥኩ።ለመጀመሪያ ቀን በእንደዚያ አይነት ሰላምታ ሰላም የተባልኩት በዛች ሴት ይመስለኛል።ማንም በእንደዚያ ባለ አክብሮትና ትህትና እጅ ነስቶኝ አያውቅም ነበር።ጨዋነቷ ምንም የማታውቅ እንደሆነች እንዳስብ አደረገኝ።ሙድ የሌላት..በቀላሉ እጇ የምትገባ መሰለችኝ።

ፍቃድ ሳልጠይቅ አጠገቧ ቁጭ አልኩኝ።በደንብ እንዳያት እድል አገኘሁ።ያልተቀባባ፣ ያልተነካካ ጠይም መልክ አላት።በዝምታ እንዲማርክ ተፈጥሮ የሆነ ነገሯን የደፋችበት የሚመስል ጠይም መልክ።

ለምን ብቻዋን፣ ለምን በዝምታ፣ ለምን በባዶ ጠረጴዛ ፊት እንደተቀመጠች ሳይገባኝ ‹ምን ይምጣልሽ? ስል ያለልማዴ ትሁት መስዬ ጠየኳት።

‹አ..አመሰግናለው› አለችኝ።

ግብዣ የምትገፋን የመጀመሪያዋን ሴት ተዋወኩ።እዛ ቤት የሚገቡ ሴቶች ሁሉ አንትና ይከፍላል እያሉ የሚጠጡ ናቸው። እኔን ተማምነው በሌለሁበት በረከት ይከፍላል እያሉ የሚጠጡ እንኳን ብዙ ናቸው።ይቺ ሴት ግን አመሰግናለው አለችኝ።የባሰ ተገረምኩባት..መቼም መጠጥ ጠጥቼ አላውቅም ትለኝና ቀን ሙሉ ስስቅ እንዳልውል እያልኩ እያሰብኩ ‹ቢራ የማይመችሽ ከሆነ ሌላ ማዘዝ ትችያለሽ..! ከማለቴ..

‹ይቅርታ መጠጥ አልጠጣም።አለችኝ..

ተመስጌን..በህይወቴ አንድ የማትጠጣ ሴት ተዋወኩ ስል ለራሴ አወራሁ። ሳወራ ሰምታኝ ኖሮ ዞራ አየችኝ።ግን ምንም አላለችኝም።የፈለገችውን ብትለኝ በወደድኩ ነበር።ለምትለኝ ለየትኛውም ነገር የተዘጋጀ ልብና አእምሮ ነበረኝ።ካላወሯት የማታወራ ነፍስ አለቻት..ዝም ካሏት እስከመቼም ዝም የምትል።ቢያንስ እዛ ቤት ለምን እንደመጣች ማወቅ ፈልጌአለው..

‹ካልጠጣሽ ለምን...ገና ሳልጨርሰው

‹ሰው እየጠበኩ ነው..› ስትል መለሰችልኝ። እንድታወራኝ ለማድረግ ያለኝ የመጨረሻ አማራጭ ያ ነበር ገና አውርቼ ሳልጨርስ ከአፌ ላይ ተቀበለችኝ። ዝም ማለት የሚያስደስታት ስለመሰለኝ ያለልማዴ ዝም ልል ተገደድኩ። ግን ዝም ማለት አልቻልኩም..ተቁነጠነጥኩ። ወዲያው የእጅ ስልኳ ጠርቶ በምልክት ቻው ብላኝ በተቀመጥኩበት ጥላኝ ሄደች።

በነጋታው ቅዳሜ ረፋድ ላይ በስሱ ነክሼ፣ ማወራረጃ ጠርሙስ ጨብጬ ቁጭ ባልኩበት አንድ ሰው ከውጪ ጠራኝ። ማንም በሙሉ ስሜ ጠርቶኝ አያውቅም። ቤካ ነው የሚሉኝ። ያን ቀን ግን ስሜን በሙሉ ሰማሁት። ስሜ በሙሉ ሲጠራ ምን እንደሚመስል ያን ቀን ነው የታዘብኩት።ማን አባቱ ነው በሙሉ ስሜ የሚጠራኝ በሚመስል አይነት እየተጣደፍኩ ወደ ውጪ ወጣሁ። ይቺው ጠይም ሴት ናት ብል ማን ያምነኛል? አዎ ራሷ ናት። ስሜን እንዴት እንዳወቀችው፣ በዛ ጠዋት እዛ ቤት ይገኛል ብላ እንዴት እንዳሰበች ለማሰብ ጊዜ አላገኘሁም። በመጠጥ የሚሰነፍጥ አፌን ይዤ ፊቷ ቆምኩ።

‹ሰላም! አለችኝ በትላንቱ አኳኋን ግራ እጇን ቀኝ እጇ ላይ አሳርፋ ከወገቧ ዝቅ በማለት።አፌ ውስጥ ያለው ጫት ትን ሊለኝ ምንም አልቀረኝ።በዛ ጨዋነት እኔን ሰላም ለማለት ማጎንበሷ ከትላንቱ የባሰ እንድደነቅባት አደረገኝ..።ሳላውቀው ተሳብኩባት..

‹ደብሮኛል..አብረኸኝ ወክ የምታደርግ ከሆነ? ስትል አይን አይኔን እያየች ጠየቀችኝ።አይናፋር መስላኝ ነበር ቅዳሜ መጥቶ..ከመሰል ወዳጆቼ ጋር ተቀምጬ ምንም የማላስበው ሰው ያን ቀን ከዛች ሴት ጋር ወክ ለማድረግ ተስማማው።ራሴን ተጠራጠርኩት..የማላውቀውን ራሴን በራሴ ውስጥ አገኘሁት።

ሁሉን አስረስታ እስከ ምሳ ሰዐት ድረስ ወክ አደረግን።ምሳ ሰዐት ላይ ጥሩ የሚባል ምግብ ጋበዘችኝ። ከሀጢዐት በቀር ምንም የማያዝናናኝ ሰው በእሷ ተዝናናሁ።ከሮዛ ጋር በእንዲያ ባለው አጋጣሚ ተዋወቅን።ከዛች ቅዳሜ ጀምሮ ብዙ ወኮችን፣ ብዙ ምሳዎችን፣ ብዙ ጊዘኤዎችን አብረን ተጋራን። እንዳላፈቅራት ስሰጋ ምኔ እንደጠለፋት አላውቅም ወዳኝ አገኘኋት። መወደዴን ሳውቅ የትም አትሄድም ብዬ ወደነበርኩበት ሀጢዐት ተመለስኩ። ጠዋት ቁርስ ልትሰራልኝ ቤቴ ስትመጣ ከሴት ጋር ተኝቼ ነው የምታገኘኝ። እንደዛም ሆኖ ቁርስ ሳትሰራልኝ ሄዳ አታውቅም። ማታ ሰክሬ ብዙ ነገር አደርጋታለው። ሳልሰድባትና ሳላዋርዳት ቤት ገብቼ አላውቅም። ስለ እኔ ከምተሰማው በላይ ብዙ አይታለች።ግን ልትጠላኝ አልቻለችም። ከአምስት አመት እንዲህ መሆን በኋላ ቬሎ ከለበሰ ጎኗ በሙሽርነት ቆምኩ። እንዴትና ለምን እንዳገባችኝ አላውቅም..አለ የተባለን በደል ሁሉ ነው የፈጸምኩባት። በእብለትና በውሸት የወነበድኩባት እነዛ አምስት የውንብድና አመታት እግዜር ፊት በወንጀለኝነት የሚያቆሙኝ..ገሀነምንም የሚያስፈርዱብኝ ይመስለኛል። ይሄ ካልሆነና እግዜር ስለ እሷ ካልቀጣኝ ለዳግም ህይወትም ካበቃኝ ስለ ፍቅሯ ቀሪ ዘመኔን ብዙ እሆናለው ስል ነበር። ስራዬ ነው መሰለኝ ብዙ ይቅርታ ያላትን ነፍሷን እፈራት ጀመር። ከመላዕክት ጋር እንጂ ከሴት ጋር የምጋባ አልመስለልህ አለኝ።

የሰርጋችን ቀን ብቻችንን የምንሆንበትን ጊዜ ጠብቄ ግን ለምን አገባሽኝ? ስል ጠየኳት።

‹ሁሉ ነገር ተራ እንደሆነ ሲገባህ የእኔ እንደምትሆን ስለማውቅ› አለችኝ። እንግዲህ ይቺ ጠቢብ ናት ያን ወፍ ዘራሽ ያገባችው። የማልመጥናት ሰው እኮ ነኝ..ከእንግዲህ እመጥናት ይሆናል እንጂ እስካሁን እዚህ ግባ የምባል አልነበርኩም። እውነት ነው ሁሉ ነገር ተራ እንደሆነ ስናውቅ የምንመለስበት አንድ ነገር ይኖራል። እኔም እነዛ ጓደኞቼ የእሷ ያክል ደስታ አልሰጡኝም ነበር። እንዳለችውም አለም በቃኝ ብዬ በእግዜር ፊት፣ በአለም ፊት ቃሌን እሰጣታለው።

# ዓለም አቀፍ



## ኤሎን መስክ የትዊተር ሠራተኞች ረዥም ሰዓት መሥራት ካልቻሉ እንዲለቁ ጠየቀ

በቅርቡ ትዊተርን የገዛው ኤሎን መስክ ሠራተኞቹ “ለረዥም ሰዓት በከፍተኛ ጥንካሬ” ለመሥራት ቁርጠኝነት ከሌላቸው ኩባንያውን እንዲለቁ መናገሩን ሪፖርቶች ይፋ አደረጉ። አዲሱ የማኅበራዊ ድርጅት ባለቤት ለሠራተኞች በላከው ኢሜል ሠራተኞቹ በኩባንያው መቀጠል ከፈለጉ በዚህ ዓይነት አሠራር ለመቀጠል ቃል መግባት እንዳለባቸው ማሳሰቡን ዋሽንግተን ፖስት ዘግቧል።

በኩባንያው አሠራር የማይስማሙና እስከ ሐሙስ ያልፈረሙ የሦስት ወር የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚሰጣቸው መስክ ተናግሯል። ቢቢሲ የትዊተርን ምላሽ ለማካተት ኩባንያውን አስተያየቱን ጠይቆ ነበር። ዘጋርዲያን ባየውና ኤሎን መስክ ለሠራተኞቹ በጻፈው ኢሜል ትዊተር ስኬታማ ለመሆን ወጣ ያሉ ጥብቅ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለበት መናገሩም ተዘግቧል።

“ይህ ማለት ለረዥም ሰዓታት በከፍተኛ ጥንካሬ መሥራት ማለት ነው። በልዩ ሁኔታ የኩባንያውን ሥራ በብቃት የሚያከናውኑ ሠራተኞች ብቻ በድርጅታችን ቀጣይ ይሆናሉ” ብሏል። ሰራተኞቹ “የአዲሱ ትዊተር አባል” መሆን ከፈለጉ ሐሙስ እስከ 11 ሰዓት ድረስ መፈረም እንደሚጠበቅባቸው ተነግሯቸዋል።

አክሎም “ምንም ዓይነት ውሳኔ ብትወስኑ ትዊተርን ስኬታማ ለማድረግ ላደረጋችሁት ጥረት እናመሰግናለን” ብሏል። የዓለማችን እጅግ ባለጸጋው መስክ ኩባንያውን በ44 ቢሊየን ዶላር ውል ከገዛ በኋላ ግማሽ የሚሆኑት የትዊተር ሠራተኞች እንደሚለቁ አስታውቋል።

መስክ ኩባንያው በቀን 4 ሚሊዮን ዶላር እየከሰረ በመሆኑም ሠራተኞቹን ከመቀነስ ውጭ ምንም ምርጫ እንደሌለው አስረድቷል።“ለገቢው ከፍተኛ ማሽቆልቆልም፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የማስታወቂያ ኩባንያዎች በማኅበራዊ ድረ ገጹ ላይ እንዳያስተዋውቁ ጫና ማሳደራቸው ነው” ሲል ወቅሷል።

መስክ ድርጅቱን መግዛቱን ተከትሎ በርካታ ከፍተኛ የትዊተር ሥራ አስፈፃሚዎች ከሥልጣናቸው ተነስተዋል። ባለፈው ሳምንትም ኤሎን መስክ ለትዊተር ሠራተኞች እንደተናገረው የኩባንያውን ሥራ ከቤት ሆኖ መሥራት እንደሚያበቃና “አስቸጋሪ ጊዜያት” ወደፊት እንደሚጠብቃቸው ሪፖርቶች ገልጸዋል። ኤሎን መስክ ለሠራተኞች በላከው ኢሜል ሠራተኞች በሳምንት ቢያንስ ለ40 ሰዓታት በቢሮ ውስጥ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ተናግሯል ሲል ብሉምበርግ መዘገቡን ጠቅሶ ቢቢሲ ዘግቧል።

## ኔቶ ፖላንድ የተመታችው በዩክሬን ሚሳኤል ሊሆን ይችላል አለ



ፖላንድ ውስጥ ሁለት ሰዎችን የገደለው ሚሳኤል የዩክሬን ሊሆን እንደሚችል የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃልኪዳን (ኔቶ) ዋና ጸሐፊ የሆኑት ጀነራል ጄን ስቶልንበርግ ገለጹ።

በዩክሬን ድንበር አቅራቢያ ስለተተኮሰው ሚሳኤል ምርመራ እየተደረገ ሲሆን፣ ዋና ጸሐፊው “ሚሳኤሉ የዩክሬን የአየር መከላከያ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው” ብለዋል። ሚሳኤሉ የዩክሬን ቢሆንም፣ ለአጠቃላይ ሁኔታው ተጠያቂ ሩስያ እንደሆነች ተናግረዋል። ሚሳኤሉ የተተኮሰው በሩሲያ እንደሆነ ዩክሬን ገልጻለች።“ይሄ የእኛ ሚሳኤል እንዳልሆነ ቅንጣት አልጠራጠርም። ወታደራዊ ሪፖርቶቻችን እንደሚያሳዩት ሚሳኤሉ የሩሲያ ነው” ሲሉ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ተናግረዋል።

ከዩክሬን ድንበር በስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ፣ በፖላንድ፣ ፕርዝዎዶ በተባለ የእርሻ ቦታ የወደቀው ሚሳኤልን በተመለከተ በሚደረገው ምርመራ ለመሳተፍ ዩክሬን ጠይቃለች። ሩሲያ ባለፈው ማክሰኞ ከዘጠኝ ወራት በፊት ጦርነቱ ከተጀመረ ወዲህ ትልቁ የተባለ ተከታታይ የሚሳኤል ድብደባ ዩክሬን ላይ ፈጽማለች።

ይህንን ተከትሎም ማክሰኞ የዩክሬን የአየር መከላከያዎች አልግሎት እየሰጡ ነበር። ሩሲያ በርካታ ሚሳኤሎችን ብትተኩስም ዩክሬን መታ እንደጣለቻቸው አስታውቃለች። የኔቶ አባል በሆነችው ፖላንድ ውስጥ ሚሳኤል መተኮሱ ጦርነቱ በአስጊ ሁኔታ እየተባባሰ መምጣቱን ይጠቁማል ተብሎም ተፈርቷል።

የኔቶ ዋና ጸሐፊ እንዳሉት፣ ኔቶ ዘመነኛ የአየር መከላከያዎችን ለዩክሬን ለመስጠት ቃል ገብቷል። “ዩክሬንን ከሚደግፉ የኔቶ አጋሮች ጋር ባደረግነው ውይይት ዘመናዊ የአየር መከላከያ መሣሪያዎችን ለመስጠት ተስማምተናል። መሣሪያዎቹ የሩሲያን ሚሳኤል መተው ይጥላሉ” ብለዋል። ዘላቂ መፍትሄ የሚሆነው ግን ጦርነቱን ማቆም እንደሆነ ዋና ጸሐፊው አስምረውበታል።

የፖላንድ ፕሬዚዳንት አንድርዜጅ ዱዳ፣ ከጥቃቱ ጀርባ ያለው S-300 የተባለው የሩሲያ ሚሳኤል እንደሆነ ተናግረዋል። ሆኖም ግን የተሰነዘረው ከሩሲያ እንደሆነ ማስረጃ አልተገኘም ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት





## የኦሮሚያ ትምህርት ቤቶች የእግር ኳስ ውድድር እየተካሄደ ነው

**ቦጋለ አበበ**

የኦሮሚያ ትምህርት ቤቶች የእግር ኳስ ውድድር በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስቴድየም እየተካሄደ ነው። አስራ ስድስትና ከዚያ በታች እድሜ ላይ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል በሁለቱም ጾታ በሚካሄደው ውድድር ከኦሮሚያ ክልል የተውጣጡ በርካታ ትምህርት ቤቶች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

ውድድሩ ከትናንት በስቲያ ሲጀመር በስፍራው ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ውድድሩ ፓንአፍሪካኒዝምን ለማጠናከር የሚካሄድ መሆኑን ገልጸው፣ በእያንዳንዱ ክልል መሰል ውድድሮች ተካሂደው በአገር አቀፍ ውድድር ከተለዩ በኋላ ዩጋንዳ ላይ በሚካሄደው የፓንአፍሪካኒዝም ውድድር ላይ ኢትዮጵያን እንዲወክሉ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል። እንደ ኃላፊው ገለጻ፣ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ይህን ውድድር ሲያካሂድ ዋንጫ ለማሸነፍ ብቻ ሳይሆን የፓንአፍሪካኒዝም ጽንሰ ሃሳብ በተማሪዎች ውስጥ በደንብ እንዲሰርጽ ለማድረግ ታስቦ ነው እየተካሄደ የሚገኘው። በቀጣይ አህጉሪቱን የሚመሩት ተማሪዎች እንደመሆናቸው አፍሪካ በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ባህልና ሌሎችም ዘርፎች ጠንክራ እንድትወጣ ተማሪዎች ላይ መስራት ያስፈልጋል። መሰል ውድድሮችም ለዚህ አስተዋጿቸው ትልቅ በመሆኑ በስፋት እየተሰራባቸው ይገኛል። "ተማሪዎች የነገ አገር ተረካቢና ገንቢዎች ናቸው፣ አባቶቻችን የተጠናከረች አፍሪካን ለመገንባት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፣ ይህን ታሪክ ተማሪዎች አጠናክረው እንዲቀጥሉና ኃላፊነት ለመውሰድ እንዲዘጋጁ ማሳሰብ እፈልጋለሁ" ያሉት ኃላፊው ይህ የፓንአፍሪካኒዝም ውድድር እግር ኳስ



ከመላው ኦሮሚያ የተውጣጡ ትምህርት ቤቶች በውድድሩ እየተሳተፉ ይገኛሉ፣

ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ቢሆንም በቀጣይ በሌሎች ስፖርቶችም ለማስፋት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። ለዚህም ትምህርት ቢሮው ከክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ጋር በጋራ ለመስራት የስምምነት ሰነድ እንደሚፈራረም ተናግረዋል። የዚህ ስምምነት አላማም ስፖርትን ከትምህርት ቤቶች ለመጀመር የሚያስችል ነው። በዚህም በሃያ የስፖርት አይነቶች በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውድድሮችን ለማካሄድ ይረዳል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ከዚህ ዓመት ጀምሮ በዘላቂነት እንደሚቀጥል ኃላፊው አስረድተዋል።

የኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሰሚራ አብደላ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት አስተያየት፣ ከአመት በፊት የፓን አፍሪካኒዝም የእግር ኳስ ውድድር ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ የተሳተፈ ትምህርት ቤት ከኦሮሚያ ክልል መመረጡን አስታውሰዋል። ዘንድሮም በአገር አቀፍ ውድድር ላይ ክልሉን የሚወክል ትምህርት ቤት ለመምረጥ በአዳማ ውድድር እየተካሄደ መሆኑን ኃላፊዋ ጠቁመው ይህም በአፍሪካ መድረክ ኢትዮጵያን የሚወክል ትምህርት ቤት ዳግም ከዚሁ ክልል ለማስመረጥ የሚደረገው ጥረት አንድ አካል መሆኑን አስረድተዋል። ከዚህ በፊት ለረጅም ዓመታት በአገር አቀፍ ደረጃም እንደ ክልልም የትምህርት ቤቶች ውድድር ሲካሄድ መቆየቱን የጠቆሙት ኃላፊዋ፣ በ2011 ዓ.ም አገር አቀፉ የትምህርት ቤቶች ውድድር መቀሌ ላይ ከተካሄደ በኋላ 2013 ላይ መካሄድ የነበረበት ቢሆንም በኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰት ሳይካሄድ መቅረቱን ጠቅሰዋል። ዘንድሮ ግን በአዲስ መልክ ቢሮው ሰነድ አዘጋጅቶ ከትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር ውድድሩን ማካሄድ ችሏል። "በስፖርት ትልቁ ተስፋ የሚገኘው ታዳጊዎች ላይ ነው፣ ታዳጊዎችን ለማግኘት ደግሞ ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት አድርገናል" ያሉት ወይዘሮ ጠይባ በክልሉ ከስር ጀምሮ በእያንዳንዱ የመዋቅር ደረጃ ውድድሮች በስፋት እንደሚካሄዱ አስረድተዋል። ለዚህም ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል ሰነድ ከትናንት በስቲያ ተፈርሟል።

የፓን አፍሪካኒዝም የእግር ኳስ ውድድር ከዓመት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በኮንጎ ሲካሄድ ኦሮሚያ ክልል የአምቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢትዮጵያን ወክሎ እንዲወዳደር ማስመረጥ ችሏል። በዚያም ውድድር ክልሉ ጥሩ ተፎካካሪ በመሆን አራተኛ ደረጃን ይዞ ከማጠናቀቅ ባለፈ ጥሩ ልምድ ይዞ መመለሱን ኃላፊዋ ተናግረዋል። በፊፉም ሰዎች በተለይም ከእድሜ ተገቢነት አኳያ አድናቆት ማግኘታቸውን ተናግረዋል። "የኦሮሚያ ክልል በሁሉም ስፖርቶች እምቅ አቅም አለው፣ ከእኛ የሚጠበቀው ይህን እምቅ አቅም አውጥቶ መጠቀም ነው" ያሉት ኃላፊዋ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚወክሉ ታዳጊዎችን ለማፍራት ቢሮው ሰፊ ስራ እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለፃ፣ ትምህርት ቤቶች ሲመሰረቱ የስፖርት ሜዳዎች አላቸው፣ እነዚህን የስፖርት ሜዳዎች ተማሪዎች ከትምህርት ቀን ውጪም ክፍት ሆነው በነፃነት እንዲጠቀሙባቸው ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የስፖርት ባለሙያዎችም እውቀታቸውን እንዲያካፍሉና ስፖርትን እንዲያስፋፉ ይፈለጋል፡፡ ከዚያ ባሻገር ቢሮው የማህበረሰብ ስፖርትን የማስፋት ፍላጎት አለው፣ ለዚህም ተማሪዎች ልምዱን እንዲያዳብሩ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ከትምህርት ቢሮው ጋር እንደተፈረመ ኃላፊዋ አስረድተዋል፡፡

ethio telecom

## Invitation to National competitive Bid

**FLOATING DATE: AS OF NOVEMBER 21, 2022**

**RFQ No: 4231699**

1. Ethio telecom invites all interested and eligible bidders by this **National Competitive Bid (NCB)** for the procurement of **"Transformers' Major Maintenance 15KV/25KVA, 15KV/50KVA, 15KV/100KVA, 33KV/25KVA and 33KV/50KVA" with RFQ No. 4231699.** The Tender remains floating from **November 21, 2022** to **December 12, 2022.**

| Item/descriptions | QTY | Unit | RFQ No | Bid Securing Amount | Type of Contract |
|---|---|---|---|---|---|
| Transformers Major Maintenance 15KV/25KVA,15KV/50KVA,15KV/100KVA,33KV/25KVAand 33KV/50KVA | 240 | Pcs | 4231699 | 200,000.00 | The type of contract to be entered and signed shall be a One-time. |

2. Bid documents can be obtained from ethio telecom's web sites, www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of Birr ***100.00 (Birr One hundred only)*** by using tele birr payment platform.

In addition, If you are interested to be on the supplier list of ethio telecom please register using the following link or copy and paste the link on a browser "https://erp.ethiotelecom.et/OA_HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".

**2.1. Sealed bids marked as**: "Tender for the Supply **Transformers' Major Maintenance 15KV/25KVA, 15KV/50KVA, 15KV/100KVA, 33KV/25KVA and 33KV/50KVA with RFQ No. 4231699** and be addressed to:

**Ethio telecom,**
**Head Quarter**
**Supply Chain Division**
**2nd Floor, Room No.211B,**
**P. O. Box 1047,**
**Addis Ababa, Ethiopia**

2.2. Bid proposal will be received at Ethio telecom, **Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on December 12, 2022 5:00 P.M.** Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.

3. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives **on December 13, 2022** at **10:00 A.M, at Ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No.210.**

4. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.

5. **Partial bid is not allowed.**

**Ethio Telecom**

ethio telecom

**INVITATION TO NATIONAL COMPETITIVE BID**

**FLOATING DATE: NOVEMBER 21,2022**

RFQ NO, 4231716

1. Ethio telecom invites all interested and eligible bidders by this **National Competitive Bid (NCB)** for the procurement of executive chair **RFQ No 4231716.** The Tender remains floating from November 21,2022 to December 12,2022.

| No. | Item/descriptions | QTY | Unit | RFQ No | Bid Security Amount |
|---|---|---|---|---|---|
| **1** | **executive chair** | **65** | **PCS** | **4231716** | **40,000** |

Bid documents can be obtained from ethio telecom's web sites www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of **Birr 100.00 (Birr One hundred only)** by using tele birr payment platform.

In addition, If you are interested to be on the supplier list of ethio telecom please register using the following link or copy and paste the link on a browser "https://erp.ethiotelecom.et/OA_HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".

2 . Interested eligible bidders may obtain further information from ethio's website (i.e. https://www.ethiotelecom.et/tender/).

a. **Sealed bids marked as:** "Tender for the Supply of executive chair with **RFQ No. 4231716** and be addressed to:

**Ethio telecom,**
**Head Quarter**
**Supply Chain Division**
**2nd Floor, Room No.211B,**
**P. O. Box 1047, Addis Ababa, Ethiopia**

b. Bid proposal will be received at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on December 12,2022 until 5:00 P.M. Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.

3. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives on December 13,2022 at 10:00 A.M, at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No.201A.

4. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.

**Ethio Telecom**